
ሒሳብ ትምህርት

የተማሪ መጽሐፍ



1ኛ ክፍል

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ሒሳብ ትምህርት

የተማሪ መጽሐፍ

አንደኛ ክፍል

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ

ሒሳብ የተማሪው

መጽሐፍ

አንደኛ ክፍል

አዘጋጆች፡ ሙሉቀን መንግስቱ (MSc)

ዉብሸት የሺጥላ (MSc)

ሀብታሙ መኮንን (BEd)

አርታኢ፡ ኡርማሌ ገደኖ (MSc)

ጥራት ተቆጣጣሪ፡ ዳንኤል በፍቃዱ (MSc)

ገምጋሚ፡ ቤተ ሞገስ (MSc)

ንጉሴ ቶማስ (MA)

መግቢያ

ይህ ለ1ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የሒሳብ ትምህርት መጽሐፍ ነው፡፡ የዚህ ክፍል ተማሪዎች ትንሽ ትንሽ ማንበብና መጻፍ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ማንበብና መጻፍ ለዚህ ክፍል ሕፃናት ከባድ ሥራ መሆኑ ገና አልቀረም ፡፡ ተማሪዎች የ1ኛ ክፍል ሒሳብ መጽሐፍን እንዲጠቀሙ የመምህሩ እና የወላጅ ድጋፍ እና ክትትል ይጠይቃል፡፡

አዳዲስ ትምህርቶችና ስሌቶች መጽሐፉ ውስጥ ተገልጸዋል፡፡ ነገር ግን መምህሩ በተጨማሪ ትምህርቱን በጥንቃቄ አዘጋጅቶ ካላቀረበላቸው ተማሪዎች ሊገባቸው አይችልም፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡት መግለጫዎች ሁሉ ምን ማስተማር እንደሚገባህ ለማሳየት ብቻ ነው፡፡

ለየመልመጃው የተሰጡትን መግለጮች ወይም መምሪያዎች ሁሉ መምህሩ እያነበበ በጥንቃቄ ማስረዳት ይገባዋል፡፡

ተማሪዎቹ ራሳቸው አንብበው እንደሚረዱ የታመነና የተረጋገጠ ካልሆነ መምህሩ ፕሮብሌሞችንና መልመጃችን ሁሉ እራሱ እያነበበ ማስረዳት ይገባዋል፡፡ በንባብና በጽሕፈት ችሎታቸው ጉድለት የሂሳብ ትምህርት እንዳይከብዳቸው ከዚህ ጉድለት የሚመጣውን ችግር ሁሉ መምህሩ እያነበበላቸውና እየጻፈላቸው ማቃለል ተግባሩ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ቢቸገሩም ችግራቸው ከሥሬቱ ብቻ መሆን አለበት፡፡

በዚህ መጽሐፍ የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉ ለ1ኛ ክፍል ሒሳብ መጽሐፍ የተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ይህ መጽሐፍ ብዙ ጠቃሚ ምክሮችን ለቃል ስሌት የተስማሙ መልመጃችንና መልሶችን የያዘ መምሪያ ነው፡፡

በመጨረሻም ይህንን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ ተጠቀሙበት፡፡ ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤቱ ንብረት ነው፡፡ ጉዳት እንዳታደርሱበት ወይም ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቁ፡፡

ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምዕራፍ-1፡ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

1.1 ከ1 እስከ 5 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች..... 1
1.2 ከ 6 እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች..... 4
1.3 ከ 1 እስከ 5 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ..... 6
1.4 ከ 6 እስከ 9 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ..... 16
1.5 ዜሮ ቁጥር..... 21
1.6 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች..... 23
1.7 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ..... 25

ምዕራፍ-2፡ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና ቅደም ተከተሎቻቸዉ

2.1 ሁለት ሆሄያትን ማወዳደር..... 29
2.2 ቀዳማይና ተከታይ ቁጥሮች..... 34
2.3 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተሎቻቸዉ..... 35
2.4 ቁጥሮችን በ 10 ምድብ መመደብ..... 37

ምዕራፍ-3: ድምራቸዉ ከ20 የማይበልጡ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

3.1 መደመር..... 41
3.2 በቁጥር መስመር መደመር..... 45
3.3 5፣6፣7፣8፣9 እና 10 በሁለት ቁጥሮች ድምር መግለጽ 48
3.4 አንድን ቁጥር በሁለት ቁጥሮች ድምር መፃፍ..... 50
3.5 ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር..... 52
3.6 ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መደመር..... 54
3.7 ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር..... 57

ምዕራፍ-4፡ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

4.1 ከ20 ጀምሮ ያሉ ቁጥሮችን ከ ላይ ወደ ታች መቁጠር..... 62
4.2 መቀነስ..... 63
4.3 ቁጥሮችን በማቀናነስ መፃፍ..... 65
4.4 ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ..... 66
4.5 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ..... 69
4.6 የመደመርና የመቀነስ ዝምድና..... 70
4.7 የቃላትፕሮብሌሞች..... 72

ምዕራፍ-5፡ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር

5.1 በአስር ምድብ መቁጥር..... 74
5.2 እስከ 100 ያሉ መሉ ቁጥሮችን መቁጠር..... 79
5.3 የቁጥሮች ቅደም ተከተል..... 84
5.4 የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓት..... 87

ምዕራፍ-6፡ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

6.1 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር መደመር..... 93
6.2 ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን መቀነስ..... 95
6.3 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን መደመር..... 99
6.4 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን መቀነስ..... 102
6.5 የቃላት ፕሮብሌሞችን መደመርና መቀነስን በመጠቀም ማስላት..... 105

ምዕራፍ-7፡ ቅርፆች

7.1 ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን መለየት..... 109
7.2 ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን መሳል..... 113
7.3 ምስሎችን በስም መዘርዘር..... 116

ምዕራፍ-8፡ ሥርዓተ ጥለት

8.1 ደጋግሞ መጣል..... 125
8.2 ደጋግሞ መጣልን ማስቀጠል..... 127
8.3 አምሳያን ደጋግሞ መጣል..... 128

ምዕራፍ-9፡ የርዝመት፤የክብደትና የመጠን መለኪያ

9.1 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ..... 132
9.2 ርዝመትን ማነፃፀር..... 133
9.3 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ..... 137
9.4 ክብደትን ማነፃፀር..... 138
9.5 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የመጠን መለኪያ..... 143
9.6 መጠንን ማነፃፀር..... 144

ምዕራፍ-10፡ የኢትዮጲያ ገንዘብ

10. 1 የኢትዮጲያ ሳንቲሞችና የብር ኖቶች..... 150
10. 2 የሳንቲሞችና የብር ኖቶች ዝምድና..... 155
10. 3 ፕሮብሌሞችን መስራት..... 157

ምዕራፍ-11፡ የኢትዮጲያ ጊዜ

11. 1 በኢትዮጲያ በቀን ዉስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያት..... 160
11. 2 የሳምንቱ ቀናት..... 163
11. 3 የቃላት ፕሮብሌም መሥራት..... 164

ምዕራፍ 1

እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

መግቢያ፡ በዚህ ምዕራፍ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር፣ ማንበብና መፃፍ፣ እንዲሁም ሙሉ ቁጥሮችን ከአቻ ምስሎች ጋር ማዛመድን ይማራሉ።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ።
- እስከ 20 ባሉ ሙሉ ቁጥሮችና መጠናቸው መካከል ያለውን ዝምድና ይረዳሉ።
- የአባላትን ብዛት በቁጥር ይገልጻሉ።

1.1 ከ1 እስከ 5 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮች

መግቢያ፤- በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከ $1-5$ ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መቁጠር፣ እንመለከታለን።



ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ 1 እስከ 5 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን በስም ትጠራላችሁ።

ተግባር 1

ከዚህ በታች የሚታዩት ምስሎች ምንድናቸዉ?

- በማየት ብዛታቸዉን ተናገሩ?

መልመጃ-1

የሚከተሉትን ምሥሎች ከነብዛታቸው ግለፁ

ምሳሌ-1	
	
አንድ ማንኪያ	ሁለት ሙዞች

	
_____	_____
	
_____	_____
	
_____	_____

በመቁጠር ብዛትን መግለፅ


መልመጃ-2

የምሥሎችን ብዛት ከሥር በተሰጠው ባዶ ቦታ ግለፁ፡፡


ምሳሌ፡



ሦስት መኪኖች




አምስት አበባዎች



_____አበባዎች



_____የቡና ስኒ



_____ጉንጥላዎች



_____ወፎች

1.2 ከ6 እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከ 6 – 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መቁጠር፣ እንመለከታለን፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ 6 እስከ 9 ላሉ ቁጥሮች መጠናቸዉን በትክክል ይስቀምጣሉ

መልመጃ-3

1) በእያንዳንዱ ሳጥን ዉስጥ ያሉት ምሥሎች ብዛት ስንት ነው?





በመቁጠር ብዛትን መግለፅ

መልመጃ-4

የምሥሎችን ብዛት ከሥር በተሰጠው ባዶ ቦታ ግለፁ፡

:

ምሳሌ፡	 ስድስት መኪኖች	 አምስት አበባዎች

	
_____አበባዎች	_____ጉንጥላዎች
	
_____ሙዞች	_____ወፎች

1.3 ከ 1 እስከ 5 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከ 1 – 5 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መቁጠር፣ ማንበብ እና መጻፍ እንመለከታለን፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ 1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን በትክክል ያነባሉ ይጽፋሉ

ቁጥር 1 ን ማንበብና መፃፍ

1 አንድ

1 1 1 1

በተለያዩ ቀለማት አጥቁሩ።



ነጠብጣቦችን በማያያዝ አድምቁ።





ደጋግማችሁ ፃፉ።



ቁጥር 2ን ማንበብና መፃፍ

2 ሁለት

ተግባር-2 የምስሎችን ብዛት ተናገሩ።


		
——የቡና ሲኒዎች	——አናናሶች	——ቡርቱኳኖች


መልመጃ፡ ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ።





በመደጋገም ፃፉ።





ቁጥር 3ን ማንበብና መፃፍ

3 ሦስት

በምሥል የሚታዩትን ቁጠሩ።

 _____ቢራቢሮዎች	 _____ዣንጥላዎች	 _____ኩባያዎች

ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ።



በመደጋገም ፃፉ።






ቁጥር 4ን ማንበብና መፃፍ

4 አራት

4 4 4 4

መልመጃ-5

ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ





በመደጋገም ፃፉ::

4 ___ ___ ___ ___ ___

4 ___ ___ ___ ___ ___

ቁጥር 5ን ማንበብና መፃፍ

5 አምስት

በምሥል የሚታዩትን ቁጠሩ።

 _____ እንቁላሎች	 _____ ላባዎች

መልመጃ-6

ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ





በመደጋገም ፃፉ።





መልመጃ-7

አንብቡ

	አንድ	1
	ሁለት	2
	ሶስት	3
	አራት	4
	አምስት	5

ከዚህ በመጀመር ወደ ታች አንብቡ

5	4	3	2	1
1	2	3	4	5

ከ1 በመጀመር ወደ ላይ አንብቡ

መልመጃ-8

የምሥሎቹን ብዛት በቁጥር ፃፉ::

ምሳሌ		4
		
		
		
		

መልመጃ-9

1. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ነጥቦችን በሳጥኑ ውስጥ አሳዩ።



ሀ)



ሐ)



ለ)




መ)




2. የሚከተሉትን ምስሎች አባላት በመቁጠር ትክክለኛውን ቁጥር አክብብ።

ሀ)



1 2 3 4 5

ለ)



1 2 3 4 5

ሐ)



1 2 3 4 5

መ)



1 2 3 4 5

3. በምሣሌው መሠረት የጎደለውን ቁጥር በሳጥኑ ውስጥ ፃፉ።



ሀ)

1		3

ለ)

3		5

ሐ)

	3	4

መ)

	2	3

ሠ)

1	2		4

ረ)

2	3		5


4. ከዚህ በታች በፊደል ለተገለጹት ትክክለኛውን ቁጥር አክብቡ።

ሀ)	አራት	3	4	5
ለ)	አንድ	2	3	1
ሐ)	ሦስት	3	5	4
መ)	ሁለት	3	2	4
ሠ)	አምስት	3	4	5

1.4 ከ 6 እስከ 9 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ


ቁጥር 6ን ማንበብና መፃፍ

ተግባር-3 የምስሎቹን ብዛት በሳጥን ውስጥ ፃፉ::



መልመጃ-11

ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ



በመደጋገም ፃፉ::





በተለያየ ቀለማት ቀቡ



ቁጥር 7ን ማንበብና መፃፍ

7 ሰባት

ተግባር- በምስሉ ላይ ስንት ድመቶች ይታያሉ?

በምስል ሲቀመጥ	በቁጥር ሲፃፍ	በፊደል ሲፃፍ
	_____	_____

መልመጃ-12

ካጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ

7	7	7	7	7	7

በመደጋገም ፃፉ::

7	—	—	—	—	—
7	—	—	—	—	—


ቁጥር 8ን ማንበብና መፃፍ

8 ስምንት

ተግባር- 4

ሀ) ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አምስት ጊዜ በመደጋገም ሰምንት በሉ።

ለ) የተሰጡትን ምስሎች በመቁጠር ብዛታቸውን ከግርጌ ጻፉ።



_____	_____	_____

መልመጃ-13

ሀ) ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቁ።




ለ) በመደጋገም ጻፉ።



ሐ) የተለያዩ ቀለሞችን በክፍት ቦታው ሙሉ።



መ) ምስሎቹን በመቁጠር ብዛቱን ከግርጌው ጻፉ። መልሱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።



ቁጥር 9ን ማንበብና መፃፍ

ዘጠኝ

ተግባር-

ሀ) በምስሉ ለይ ስንት ልጆች አሉ

በምስል ሲቀመጥ	በቁጥር ሲፃፍ	በፊደል ሲፃፍ
	9	ዘጠኝ

ለ) ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አምስት ጊዜ በመደጋገም ዘጠኝ በሉ።

9	9	9	9	9

መልመጃ-14


ሀ) ነጠብጣቦችን በማያያዝ እና ደጋግማችሁ ፃፉ።



ለ) የተለያዩ ቀለሞችን በክፍት ቦታው ሙሉ።

9	9	9	9	9	9

ሐ) ምስሎቹን በመቁጠር ብዛቱን ከግርጌው ፃፉ።

መልመጃ-15

1. በተሰጠው ክፍት ቦታ ደጋግማችሁ ፃፉ።

1 ——— ——— ——— ——— ———
2 ——— ——— ——— ——— ———
3 ——— ——— ——— ——— ———
4 ——— ——— ——— ——— ———
5 ——— ——— ——— ——— ———
6 ——— ——— ——— ——— ———
7 ——— ——— ——— ——— ———
8 ——— ——— ——— ——— ———
9 ——— ——— ——— ——— ———

2. አንብቡ

9	9	9	9	9
8	8	8	8	8
7	7	7	7	7

6	6	6	6	6
5	5	5	5	5
4	4	4	4	4
3	3	3	3	3
2	2	2	2	2
1	1	1	1	1

1.5 ዜሮ ቁጥር

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የዜሮ ጽንሰ ሀሳብን ትረዳላችሁ፡፡

ተግባር-2

በአንድ ሳጥን ውስጥ ስድስት እንቁላሎች ቢኖሩ እና እነዚህ እንቁላሎች በሙሉ ቢሰበሩ በሳጥኑ ውስጥ ስንት ያልተሰበሩ እንቁላሎች ይኖራሉ?



የመጀመሪያው ምሥል



የሁለተኛው ምሥል




የሦስተኛው ምሥል

- በመጀመሪያው ምሥል ሁለት ወፎች በወፍ ጎጆ ውስጥ አርፈው ይታያሉ፡፡
- በሁለተኛው ምሥል ከሁለት ወፎች አንዱ ተነስቶ ሲሄዱ ይታያል፡፡
- በሦስተኛው ምሥል የቀረው ሁለተኛ ወፍ ተነስቶ ሲሄዱ ይታያል፡፡አሁን በጎጆ ውስጥ ምንም ወፍ የለም፡፡ ስለዚህ ምንም ወፍ የለም የሚለውን በቁጥር ስንገልፅ 0 እንላለን፡፡

ማስታወሻ፡ ዜሮ በአንድ ስብስብ ውስጥ ምንም አባል አለመኖሩን በመጠን ለመግለጽ የምንጠቀመው ቁጥር ነው። ስለዚህ ዜሮ ቁጥር ሲሆን ባዶ ወይንም ምንም የሚለውን መጠን ይገልፃል።

ዜሮን በቁጥሮች ጨረር ላይም በሚከተለው ሁኔታ መግለጽ ይቻላል




ከላይ እንዳየነው በቁጥር ጨረር ላይ ዜሮ ሁልጊዜ ከ1 በስተግራ በኩል ትገኛለች ስለሆነም 0 ከሁሉም መቁጠሪያ ቁጥሮች ያንሳል።

ቁጥር 0ን ማንበብና መፃፍ


ዜሮ

ተግባር-6


ሀ) ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አምስት ጊዜ በመደጋገም ዜሮ በሉ።



ለ) ነጠብጣቦችን በማያያዝ እና ደጋግማችሁ ፃፉ።



ሐ) የተለያዩ ቀለሞችን በክፍት ቦታው ሙሉ።



መልመጃ-16

በፊደል ደጋግማቹ ፃፉ

በቁጥር	በፊደል
0	ዜሮ
0	
0	
0	

1.6 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

መግቢያ፡ በቀደመው ትምህርት እስከ 9 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር፣ማንበብ እና መፃፍ ተምረናል ከዚህ ቀጥሎ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን እንመለከታለን፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ ቅደም ተከተል በተናጠል ይረዳሉ

የሚከተሉትን አጥኑ

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■	10 እና 0	አሥር	10
■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■	10 እና 1	አሥራ አንድ	11
■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■	10 እና 2	አሥራ ሁለት	12

	10 እና 3	አሥራ ሦስት	13
	10 እና 4	አሥራ አራት	14
	10 እና 5	አሥራ አምስት	15
	10 እና 6	አሥራ ስድስት	16
	10 እና 7	አሥራ ሰባት	17
	10 እና 8	አሥራ ስምንት	18
	10 እና 9	አሥራ ዘጠኝ	19
	10 እና 10	ሃያ	20

መልመጃ-17

1) የጎደለውን ቁጥር ሙሉ።

ሀ. 7 ፣ 8 ፣ 9 ፣ 10 ፣_____፣_____ ፣ 13፣_____ ፣15።

ለ. 18 ፣ 17፣ 16 ፣_____ ፣_____ ፣_____ ፣ 12፣ 11።

ሐ. 11 ፣ 12 ፣ 13 ፣_____ ፣_____ ፣_____ ፣_____ ፣ 18።።

መ. 9 ፣ 10 ፣ 11 ፣_____፣ _____ ፣ _____ ፣_____ ፣ 16።።

1.7 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በፊደል ይፅፋሉ
- በአሃዝና በፊደል የተፃፉ ቁጥሮችን ያነባሉ

የሚከተሉትን አንብቡ።።

10	አሥር
11	አሥራ አንድ
12	አሥራ ሁለት
13	አሥራ ሦስት
14	አሥራ አራት
15	አሥራ አምስት
16	አሥራ ስድስት
17	አሥራ ሰባት
18	አሥራ ስምንት
19	አሥራ ዘጠኝ
20	ሃያ

መልመጃ-18

1) እያነበባችሁ ደጋግማችሁ ፃፉ።

10	10									
11	11									
12	12									
13	13									
14	14									
15	15									
16	16									
17	17									
18	18									
19	19									
20	20									

የማጠቃለያ መልመጃ

1. በምሳሌው መሠረት በፊደል ጻፉ።

ምሳሌ 8 ስምንት 11 አሥራ አንድ

ሀ) 16_____ መ) 20_____

ለ) 19_____ ሠ) 15_____

ሐ) 12_____

2. በፊደል የተሰጠውን በምሳሌ ሀ መሠረት በአሀዝ ጻፉ።


ሀ) ሰባት 7 መ) አሥራ ሰባት_____

ለ) አሥራ ሦስት_____ ሠ) አሥራ ስምንት_____


ሐ) አሥራ አራት_____ ረ) ዛያ_____

3. ባዶውን ሣጥን በትክክለኛው ቁጥር ሙሉ።


ሀ)




ለ)




ሐ)



መ)




ሠ)



4. ነጥቦችን በመቁጠር ብዛታቸውን ከሚገልፀው ቁጥር ጋር አዛምዱ።

	8
	4
	3
	1
	5

	6
	9
	7
	2

5. **ከ1 – 20 ያሉትን ቁጥሮች ከታች ወደ ላይ በመቁጠር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።።**

1				5			8	9	10
			14				18		20

6. **ከ1 – 20 ያሉትን ቁጥሮች ከላይ ወደ ታች በመቁጠር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።።**

20			17		15				
		8					3		1

ምዕራፍ-2

ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና ቅደም ተከተሎቻቸዉ

መግቢያ፡ ቀደም ባለው ምዕራፍ እስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር ማንበብ እና መፃፍ ተምረናል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥን ይማራሉ።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡


- ሁለት ቁጥሮችን ያነፃፅራሉ።
- ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸዉ ያስቀምጣሉ።


2.1 ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር


ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-


- ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸዉ መሰረት ታስቀምጣላችሁ።

ተግባር-1፡ በሣጥኑ ከተሠጡት ተመሳሳይ ምስሎች በብዛት የሚበልጠው በግራ በኩል ወይስ በቀኝ በኩል ያለው ነው?










የትኛው ስብስብ ጥቂት ኪሶች አሉት?

የትኛው ስብስብ ብዙ ኪሶች አሉት?



መልመጃ-1

በምሳሌው መሠረት የጎደለውን ቁጥር በሳጥኑ ውስጥ ፃፉ።

ምሳሌ	1		3	4		1	2	3	4

ሀ)

1		3

መ)

3		5

ለ)

	3	4

ሠ)

	2	3

ሐ)

1	2		4

ረ)

2	3		5

1. ያንሳል

አስተዉሉ፡- < የያንሳል ምልክት ነው።

ምሳሌ



1 ኪስ 1 < 3 3 ኪሶች

መልመጃ-2

ከዚህ በላይ ባለው ምሳሌው መሠረት የምስሎቹን ብዛት አወዳድሩ።

ሀ)




4 ኮከቦች




5 ኮከቦች

4 _____ 5



2 ዳክዬዎች



3 ዳክዬዎች

2 _____ 3

2. ይበልጣል

አስተዉሉ፡- > የይበልጣል ምልክት ነው።

ምሳሌ










5 ኩባያዎች 5 > 2 2 ኩባያዎች

መልመጃ-3


ከዚህ በላይ ባለው ምሳሌ መሠረት የምስሎቹን ብዛት አወዳድሩ።


ሀ) 	
2 ____ 1	
ለ) 	
5 ____ 3	
ሐ) 	
4 ____ 1	

3. እኩል

አስተዉሉ፡- = የእኩል ይሆናል ምልክት ነው።

ምሳሌ






2 ዶሮች 2 = 2 2 ዶሮች

መልመጃ-4

ከዚህ በላይ ባለው ምሣሌ መሠረት ሥሩ።

ሀ) 		
3 እርሳሶች	3_____3	3 እርሳሶች

ለ) 		
4 የሜዳ አህዮች	4_____4	4 የሜዳ አህዮች

መልመጃ-5

አሃዞችን በማወዳደር ክፍት ቦታዎችን በተገቢው ምልክት ሙሉ።

ምሳሌ	1_____3 1 < 3 2_____1 2 > 1 4_____5 4 < 5 3_____3 3 = 3

ሀ)	3 ———— 2	3 ———— 5	3 ———— 4
	4 ———— 1	1 ———— 1	4 ———— 3
ለ)	5 ———— 5	5 ———— 2	1 ———— 5
	3 ———— 3	5 ———— 4	4 ———— 4



2.2 ቀዳማይና ተከታይ ቁጥሮች

መግቢያ፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የአንድን ቁጥር ቀዳማይና ተከታይ ቁጥሮችን ይለያሉ።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- በውስጣቸው ባሉ የዕቃዎች ብዛት መሠረት ስብስቦችን ያነፃፅራሉ፤
- በቁጥር መስመር ከቁጥር በፊት፤በኃላ እና መካከል ያሉ ቁጥሮችን ያመለክታሉ

ተግባር-2፡ በስተግራ ያለዉ ይበልጣል ወይስ በስተቀኝ?

<table>
<tr><td></td><td></td><td> </td></tr>
<tr><td>ምሳሌ: </td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>1ሙዝ</td><td>2ሙዞች</td><td>3ሙዞች</td></tr>
</table>

ስለዚህ $1 < 2$ ፣ $2 < 3$ ወይም $3 > 2$ ፣ $2 > 1$ በዚህ የተነሳ 1 የ 2 ቀዳማይ ነዉ። 3 ደግሞ የ 2 ተከታይ ነዉ።

መልመጃ-6

1. ቀጥለዉ ለተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይ እና ተከታይ ፈልጉ።

ሀ) የ 9 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

ለ) የ 8 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

ሐ) የ 3 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

መ) የ 7 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

ሠ) የ 5 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

2.3 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተሎቻቸዉ

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የቁጥር መሥመርን በመጠቀም በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በቁጥር መስመር ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸዉ መሰረት ያስቀምጣሉ።

አስተውሉ፡ እስከ 10 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች ቅደም ተከተል ከትንሹ ወደ ትልቁ እንደሚከተለው ይሆናል።

1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10

መልመጃ-7

1) ተስማሚውን ቁጥሮች በባዶ ቦታዎች በመፃፍ ቅደም ተከተላቸውን አሳዩ።

ሀ.

4	5	6		8	9	

ለ.

	8		6		4	

ሐ.

	4		6			9

መ.

1	2	3		5		7		9

ሠ.

				8	9	10

ረ.

		6		4		2

2) የ $<$ ፤ $=$ ወይም $>$ ምልክቶች በመጠቀም ትክክለኛውን ምልክት ባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።

$6 < 8$	7_____9
$6 < 9$	7_____8
$6 < 7$	7_____6
$6 = 6$	7_____7
	7_____5

አስተውሉ፡ ከ 11 – 20 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች ቅደም ተከተል ከትንሹ ወደ ትልቁ እንደሚከተለው ይሆናል።

11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20

መልመጃ-8

1) ተስማሚውን ቁጥሮች በባዶ ቦታዎች በመሞፍ ቅደም ተከተላቸውን አሳዩ።

ሀ.

16	15	14		12	11		9

ለ.	18		16	15		13	12	
ሐ.	20	19		17	16		14	
መ.	19	18	17		15	14		12
ሠ.	15		13	12		10		8

2.4 ቁጥሮችን በ10 ምድብ መመደብ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች


- ሁለት የተለያዩ አሳላት ያሏቸዉን ስብስቦች በማዋሃድ አሳላትን በ 10 ምድብ ያስቀምጣሉ

ተግባር-3


የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ለተከሉት ችግኝ ለአጥር መሥሪያ ትናንሽ እንጨቶችን አምጥተዉ ነበር፡፡ መስከረም 17 ትናንሽ እንጨቶችን ብታመጣ በስንት አሥሮች እና በስንት አንዶች ማሰር ትችላለች?

<u>በአሥሮች እና በአንዶች መቁጠር</u>

ስንት አሥሮች እና ስንት አንዶች አሉን?



ከላይ የተሰጡትን ነጠብጣቦች 19 ናቸው በአሥር ምድብና በአንዶች ስናስቀምጥ



በ 19 ውስጥ 1 አሥር እና ዘጠኝ አንዶች አሉት ስለዚህ 19 = 10 + 9

መልመጃ-9

ከዚህ በታች ያሉት ቁጥሮች ስንት አሥሮች እና አንዶች እንዳሏቸዉ ግለፅ/ጪ።

ምሳሌ፡- 18 = 1 አሥር እና 8 አንዶች አሉት።

1. 16 = ___ አሥር እና _____ አንዶች አሉት?
2. 17 = ___ አሥር እና _____ አንዶች አሉት?
3. 15 = ___ አሥር እና _____ አንዶች አሉት?
4. 13 = ___ አሥር እና _____ አንዶች አሉት?



1. ባዶ ሳጥኖችን ሙሉ።

ሀ.	0	1	2	3	4	5	6	7	8	9
	10	11		13		15			18	

ለ.	8	10	12				20

2. ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ::

ሀ) 2፣4፣6፣_____፣_____ ፣_____ ፣_____ ፣16::

ለ) 3፣6፣9፣_____፣_____ ፣18::

ሐ) 0፣5፣10፣_____፣20::

3. በባዶ ሳጥኖችን ሙሉ::

የተሰጠ ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
9	–	9
6		
19	1	9
13		
14		
17		
16		

4. ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች < ፣ > ወይም = ምልክቶች አንዱን በመጠቀም በ "ሀ" መሠረት የተሰጡትን ቁጥሮች አወዳድሩ::

ሀ) 8 < 9

ለ) 12___12

ሐ) 10____8

መ) 8____10

ሠ) 11___11

ረ) 16____19

ሰ) 18____10

ሸ) 10____18

ቀ) 15____15

በ) 3____12

5. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩን አግኙ።

ሀ) 16 ለ) 5 ሐ) 10

6. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ተከታይ ሙሉ ቁጥሩን አግኙ።

ሀ) 12 ለ) 3 ሐ) 7 መ) 15


7. በተሰጡት ሁለት ቁጥሮች መካከል ያሉትን ሙሉ ቁጥሮች አንድ በአንድ በቅደም ተከተል ዘርዝሩ።

ሀ) 0 እና 4 ለ) 3 እና 8 ሐ) 10 እና 15 መ) 7 እና 13

8. ከተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀጥሎ ያሉትን አምስት አምስት ሙሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተ ል ዘርዝሩ።

ሀ) 0 ለ) 3 ሐ) 10 መ) 13

9. የቁጥር ጨዋታ፡ ከ 1 እስከ 9 ያሉትን ቁጥሮች በቅደም ተከተል በማያያዝ የተገኘዉን ምስል ቀቡ።



ምዕራፍ-3

ድምራቸዉ ከ20 የማይበልጡ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

መግቢያ፡ ድምራቸው ከ20 የማይበልጡ ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን እንዲሁም ባለ አንድ ሆሄ እና ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በተለያዩ ዘዴዎች መደመር ይቻላል።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የመደመር ምልክትንና የመደመር የሒሳብ ዐረፍተ ነገርን ለይተዉ ያዉቃሉ ።
- ድምራቸዉ ከ20 የማይበልጡ ሁለት ቁጥሮችን ይደምራሉ።

3.1 መደመር

መግቢያ፡ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንዲሁም ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ስንደምር ቁጥሮችን፣ የመደመር ምልክት እና የእኩል ይሆናል ምልክትን በመጠቀም በመደመር አረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የ “+” እና የ “=” ምልክትን ትርጉም ትረዳላችሁ።
- ሁለት የተለያዩ ስብስቦች በመቀላቀል የድብልቁን አባላት ብዛት በመቁጠር ትገልፃላችሁ።

ተግባር-1፡ የምሥሎቹን ብዛት በባዶው ሣጥኑ ውስጥ ፃፉ።

ሀ)



ለ)




ሐ)






መ)



ተግባር-1 በመጀመሪያው ምሳሌ መሠረት ከምስሎች በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ።

		
2 ኪሶች እና 3 ኪሶች በአንድ ላይ 5 ኪሶች ይሆናሉ።		

		
_____	እና _____ይሆናል_____	

		
_____	እና _____	ይሆናል_____

		
_____	እና _____	ይሆናል_____

ምሳሌ፡-በ ሀ መሠረት ክፍት ቦታውን በትክክለኛው ቁጥር ሙሉ።

ሀ) 2 እና 3 ሲደመሩ እኩል ይሆናል 5

ለ) 5 እና 2 ሲደመሩ እኩል ይሆናል----------

ሐ) 5 እና 3 ሲደመሩ እኩል ይሆናል----------

መ) 6 እና 3 ሲደመሩ እኩል ይሆናል----------

አስተውሉ፡ **ሀ. + የመደመር ምልክት ነው።**

ለ. = የእኩል ይሆናል ምልክት ነው።

እነዚህን ምልክቶች በሚከተለው ሁኔታ እናነባለን።

ምሳሌ፡- ሀ. $2 + 2 = 4$ ... ...ሁለት ሲደመር ሁለት እኩል ይሆናል አራት።

ለ. $4 + 1 = 5$ ... ...አራት ሲደመር አንድ እኩል ይሆናል አምስት።


ሐ. $3 + 4 = 7$ ... ...ሶስት ሲደመር አራት እኩል ይሆናል ሰባት።

መልመጃ-1

የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት በመደመር አረፍተ ነገር ግለጹ።

ሀ.  ___ + ___ = ___

ለ.  ___ + ___ = ___

ሐ.  ___ + ___ = ___

መልመጃ-2

1) ለሚከተሉት የቃላት ፕሮብሌሞች ዋጋቸውን ፈልግ፡፡

ሀ) አበበ ሦስት ሴት ዶሮዎች አሉት ሁሉም ዶሮዎች እያንዳንዳቸዉ በየቀኑ አንድ አንድ ዕንቁላል ይጥላሉ በዚህ መሠረት አበበ በአንድ ቀን ስንት ዕንቁላሎችን ያገኛል?

ለ) አየለች የ 1ኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ እናቷ 3 ደብተሮችን ገዙላት አባቷ ደግሞ 2 ደብተሮችን ገዙላት፡፡ እንዲሁም እህቷ 4 ደብተሮችን ገዛችላት፡፡ በጠቅላላዉ ለአየለች የተገዛዉ የደብተር ብዛት ምን ያህል ነዉ?

2. ደምሩ፡

ሀ)	$2+2+1=$____	ሠ)	$4+3+2=$____
ለ)	$4+3+2=$____	ረ)	$5+4+0=$____
ሐ)	$5+3+0=$____	ሰ)	$6+2+1=$____
መ)	$5+4+0=$____	ሸ)	$3+3+3=$____

3.2 በቁጥር መስመር መደመር

መግቢያ፡ ድምራቸው እስከ 20 የሆኑ ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን እና ባለ አንድ ሆሄን ከባለ ሁለት ሆሄት ቁጥሮች ጋር የቁጥር መስመር በመጠቀም መደመር ይቻላል፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች


- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ፡፡

ምሳሌ፡

1) $5 + 4 = ____$

በቁጥር መሥመር ላይ 5 እና 4ን ደምሩ።


መጀመሪያ በቁጥር መሥመር ላይ 5ን አሳዩ። ቀጥሎ 4 ምድብ ወደ ቀኝ ሂዱ። የደረሳችሁበት ቁጥር ድምር ይሆናል።



ስለዚህ $5 + 4 = 9$ ይሆናል።

2) $13 + 5 = ____$

በቁጥር መሥመር ላይ $13 + 5$ ደምሩ። መጀመሪያ 13ትን በቁጥር መሥመር ላይ አሳዩ።ቀጥሎ 5 ምድብ ወደ ቀኝ ሂዱ። የደረሳችሁበት ቁጥር ድምር ይሆናል።




ስለዚህ $13 + 5 = 18$ ይሆናል።

መልመጃ-3


1) በምሳሌው መሠረት የቁጥር መስመር በመጠቀም የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ።

ምሳሌ




6 + 1 = 7

ሀ.




$1 + 5 = \square$

ለ.




$2 + 8 = \square$

ሐ.



$1 + 4 = \square$


መ.



$2 + 6 = \square$


2) ከዚህ በታች ባለው ምሳሌ መሠረት፤የቁጥር መስመሩን በመጠቀም የመደመር አረፍተ ነገሩን ፃፉ።

ምሳሌ



4 + 3 = 7

ሀ.




$\square + \square = \square$


ለ.



ሐ.



መ.



3.3 5፣6፣7፣8፣9 እና 10 በሁለት ቁጥሮች ድምር መግለጽ


መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የ 5፣ 6፣ 7፣ 8፣ 9 እና 10 የመደመር ተጣማሪ የሆኑ ቁጥሮችን በመጠቀም የሁለት ቁጥሮች ድምር አድርገው መግለፅን ይማራሉ።

ተፈላጊ ብቃት፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር ትገልፃላችሁ።

አንድን ሙሉ ቁጥር የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር አድርጎ መግለጽ ይቻላል። ከዚህ በታች የቀረበውን አስራጂ ተመልከቱ፡


ምሳሌ




መልመጃ–4፡

ምሳሌውን በማጥናት የሚከተሉትን ባዶ ሳጥኖች ሙሉ፡፡


ሀ.



ለ.



ሐ.



3.4 አንድን ቁጥር በሁለት ቁጥሮች ድምር መፃፍ


መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የተሰጣቸውን ቁጥር እኩል በሆነ በሁለት ቁጥሮች ድምር መግለፅን ይማራሉ።

ተፈላጊ ብቃት፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር ትገልፃላችሁ።


አንድን ሙሉ ቁጥር የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር አድርጎ መግለጽ ይቻላል። ከዚህ በታች የቀረበውን አስራጂ ተመልከቱ፡

ምሳሌ፡ ሁለት ቁጥሮች ተደምረው 12 የሚሰጡ በመፈለግ ባዶ ሳጥኑን ሙሉ፡፡




መልመጃ-5 ከዚህ በላይ ባለው ምሳሌ መሠረት ድምራቸው የተጠቀሰውን ቁጥር የሚሠጡ ሁለት ሙሉ ቁጥሮች ፈልጉ፡፡


ሀ.



ለ.



ሐ.



3.5 ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር

መግቢያ፡ ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር ማለት በሁለት ቦታ በመጠን እኩል ተቆጥረው የተቀመጡትን ነገሮች አንድ ላይ በመቀላቀል እንደ መቁጠር ነው።

ተፈላጊ ብቃት፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ።

ምሳሌ፡



3 + 3 = 6

መልመጃ-6

1. **ምስሎችን በመቁጠር ደምሩ።።**

ሀ.



4 + 4 = ——

ለ.



2 + 2 = ——

ሐ.



5 + 5 = ——

2) ድምሩን በባዶ ሳጥኑ ሙሉ።

ሀ. 5 + 5 = ☐ ለ. 6 + 6 = ☐ ሐ. 4 + 4 = ☐

መ. 2 + 2 = ☐ ሠ. 1 + 1 = ☐ ረ. 9 + 9 = ☐

ሰ. 3 + 3 = ☐ ሸ. 8 + 8 = ☐ ቀ. 7 + 7 = ☐

3) በምሳሌው መሠረት ደምሩ

ምሳሌ፡	$2 + 3 = 2 + 2 + 1 = 4 + 1 = 5$

ሀ. 0 + 1 = ☐ ለ. 3 + 4 = ☐ ሐ. 2 + 3 = ☐

መ. 4 + 5 = ☐ ሠ. 1 + 2 = ☐ ረ. 8 + 9 = ☐

ሰ. 6 + 7 = ☐ ሸ. 7 + 8 = ☐ ቀ. 5 + 6 = ☐

3.6 ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መደመር

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ።

ተግባር-2፡ ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ

የቁጥሮችን ድምር ሙሉ ።።

+	0	1	2	3	4	5	6	7	8	9
0										
1										
2			4							
3										
4										
5							11			
6										
7										
8										
9				12						

መልመጃ-7

1) ዓረፍተ ነገሩን እውነት የሚያደርግ ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።።

ሀ. $5 + 5 =$ _____ ለ. $6 + 6 =$ _____

ሐ. $2 + 5 =$ _____ መ. $4 +$ _____ $= 12$

ሠ. ____ $+ 3 = 11$ ረ. ____ $+ 5 = 11$

2) ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ሙላ/ይ።

	+3
6	
2	
0	
5	
1	
7	
4	
9	
8	

	+2
7	
3	
9	
5	
8	
4	
6	
0	
1	

አስተውል፡ ዜሮን በአንድ ሙሉ ቁጥር ላይ ብንደምር ውጤቱ እራሱ ሙሉ ቁጥሩ ነው።

ምሳሌ፡

$4 + 0 = 4$ $0 + 1 = 1$ $7 + 0 = 7$

መልመጃ-8

1) ባዶ ቦታውን ሙሉ/ይ።

ሀ. $3 + 0 =$ _____ መ. $10 + 0 =$ _____ ሰ. $4 + 0 =$ _____

ለ. ____ $+ 0 = 5$ ሠ. $7 +$ ____ $= 7$ ሸ. $0 + 0 =$ ____

ሐ. $6 + 0 =$ _____ ረ. $1 + 0 =$ _____ ቀ. $0 + 9 =$ ____

3.7 ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር

መግቢያ፡ ድምራቸው 20 የሆነ ባለ አንድ ሆሄ እና ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በተለያዩ ዘዴዎች መደመር ይቻላል። እነዚህን ዘዴዎች በምሳሌ ከዚህ በታች ቀርበውላችኋል።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ትደምራላችሁ።

ምሳሌ፡

1. $15 + 4 = 10 + 5 + 4$
   $= 10 + 9 = 19$

2. $14 + 3 = 10 + 4 + 3$
   $= 10 + 7 = 17$

3) $16 + 2 = 10 + 6 + 2$
   $= 10 + 8 = 18$

መልመጃ-9

1) ከዚህ በላይ ያለውን ምሳሌ በመከተል ቀጥሎ ያሉትን ደምር/ሪ።

ሀ. $14 + 4 =$ _____ ሠ. $13 + 7 =$ _____

ለ. $18 + 1 =$ _____ ረ. $14 + 5 =$ _____

ሐ. $12 + 7 =$ _____ ሰ. $12 + 6 =$ _____

መ. $11 + 5 =$ _____ ሸ. $15 + 4 =$ _____

2) ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

ሀ) በአንድ ቅርጫት ውስጥ 10 አሻንጉሊቶች ነበሩ። ከበደ ሌሎች 5 አሻንጉሊቶችን በቅርጫት ውስጥ ጨመረ። አሁን በጠቅላላው በቅርጫት ውስጥ

ስንት አሻንጉሊቶች ይኖራሉ።

ለ) አበበ 12 በጎች አሉት። አባቱ ደግሞ 6 በጎች አላቸው። የአበበና የአባቱ በጎች ብዛት በአጠቃላይ ስንት ይሆናል?


አስተውሉ፡ ሁለት የተለያዩ ቁጥሮችን መደመር በሁለት ቦታ ተቆጥረው የተቀመጡትን ነገሮች አንድ ለይ በመቀላቀል እንደመቁጠር ነው።



ምሳሌ፡ የሚከተሉትን አጥኑ።

ሀ. 		
10 + **2** = **12**		

መልመጃ-10

1. ምሥሎችን በመቁጠር ደምሩ።

ሀ. 		

12 + 3 = _____		
ለ. 		
16 + 4 = _____		

2. በምሳሌው መሠረት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

8 + 1 = 9	5 + __ = 18
__+ 3 = 16	__ + 3 = 19
13 + 4 = __	14 + __ = 20

3. ትክክለኛውን ቁጥር በባዶው ሳጥኑ ሙሉ።

3 + 6 = ☐	☐ = 5 + 13
4 + ☐ = 10	3 + ☐ = 15
☐ + 6 = 16	☐ + 5 = 19
☐ + 0 = 17	1 + ☐ = 20



1. ደምሩ

0 + 0 = _____	0 + 0 + 0 = _____
2 + 3 = _____	2 + 2 + 2 = _____
4 + 5 = _____	3 + 4 + 1 = _____
1 + 8 = _____	1 + 6 + 2 = _____
2 + 6 = _____	4 + 3 + 2 = _____
5 + 2 = _____	5 + 2 + 1 = _____
6 + 3 = _____	3 + 2 + 3 = _____
4 + 0 = _____	5 + 3 + 0 = _____

2. ባዶ ቦታውን በትክክለኛዉ ቁጥር ሙሉ።

6 +2	4 +2	5 +4	8 + 2	5 + 4	7 +6

3. አስሉ

ሀ. 12 + 2 = _____ መ. 0 + 3 = _____

ለ. 3 + 5 = _____ ሠ. 7 + 2 = _____

ሐ. 6 + 3 = _____ ረ. 9 + 7 = _____

4. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ሰጡ

ሀ. አንድ ገበሬ በ 2በሬዎች እርሻ በማረስ ላይ ይገኛል። በተጨማሪም ገበሬዉ ሌሎች 5 በሬዎቹን ወደ መስክ አሰማርቷል። ይህ ገበሬ በጠቅላላዉ ስንት በሬዎች አሉት?

ምዕራፍ-4

እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

መግቢያ፡ እስከ 20 ካሉ ሙሉ ቁጥሮች ከትልቁ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ትንሹን ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንዲሁም ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር መቀነስ ይቻላል። በዚህ ምዕራፍ እነዚህን የተለያዩ ዜዴዎች እንመለከታለን።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በመደመርና በመቀነስ መካከል ያለዉን ዝምድና ያውቃሉ።
- ከ20 የሚያንሱ ቁጥሮችን ያለብድር ይቀንሳሉ።

4.1 ከ20 ጀምሮ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ከ ላይ ወደ ታች መቁጠር

መግቢያ፡ ሙሉ ቁጥሮችን ከታች ወደ ላይ ማለትም ከትንሹ ሙሉ ቁጥር ወደ ትልቁ ሙሉ ቁጥር መቁጠር እንደሚቻለው ሁሉ ከላይ ወደ ታች ማለትም ከታወቀ መነሻ ትልቅ ሙሉ ቁጥር ወደ ትንሹ ሙሉ ቁጥር መቁጠር ይቻላል።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከላይ ወደ ታች በሁለት በሁለት እና በሦስት በሦስት ትቆጥራላችሁ።

አስተውሉ፡ ከታች ወደ ላይ ስንቆጥር ተከታይ ሙሉ ቁጥር ቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩን በአንድ ይበልጣል።

1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14	15	16	17	18	19	20
እስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ከታች ወደ ላይ ሲቀመጥ																			

አስተውሉ፡ ከላይ ወደ ታች ስንቆጥር ተከታይ ሙሉ ቁጥር ከቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩ በአንድ ያንሳል።

20	19	18	17	16	15	14	13	12	11	10	9	8	7	6	5	4	3	2	1
አስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ከላይ ወደ ታች ሲቀመጥ																			

መልመጃ-1፡ የሚከተሉትን ሰንጠረገጦች ከላይ ወደ ታች በሁለት ልዩነት በመቁጠር በቅደም ተከተላቸው ባዶ ቦታውን ሙሉ

ምሳሌ፡

	20			14		10
	20	18	16	1	12	10

ሀ)

12	10		6		2

ለ)

16			10		6

4.2 መቀነስ

መግቢያ፡ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ከሚበልጠው ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንዲሁም ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ስንቀንስ ቁጥሮችን እና የመቀነስ ምልክት በመጠቀም በመቀነስ አረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የመቀነስ ምልክትን ለይታችሁ ታውቃላችሁ።

ከዚህ በታች ያሉትን ምሥሎች ተመልከቱ

		
የመጀመሪያው ምሥል	የሁለተኛው ምሥል	የሦስተኛው ምሥል

- በመጀመሪያው ምሥል ሦስት ቢራቢሮዎች በአበባው ላይ አርፈው ይታያሉ።
- በሁለተኛው ምሥል ከሶስት ቢራቢሮዎች ሁለቱ ተነስተው ሲሄዱ ይታያሉ።
- በሦስተኛው ምሥል ደግሞ ከሦስቱ አንዱ ቢራቢሮ ብቻ እንደቀረ ይታያል።
- ይህ ሁኔታ ከሦስት ላይ ሁለት ሲንቀንስ አንድ እንደሚቀር ያሳያል።

ማስታወሻ፡

“–" የመቀነስ ምልክት

" = " የእኩል ይሆናል ምልክት

ከላይ ያየናቸውን ምሥሎች ሁኔታ እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል።

- $3 - 2 = 1$.....ከ 3 ላይ 2 ሲቀነስ 1 ይቀራል።

መልመጃ-2 ፡ የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ስሩ።

1) ተስፋዬ ሦስት ብርቱካኖች ነበሩት። አንዱን ብረቱካን ለጓደኛው ቢሰጥ ስንት ብርቱካኖች ይቀሩታል?
2) ሁለት አረንጓዴ ጠርሙሶች ጠረጴዛ ላይ ነበሩ። ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ስንት አረንጓዴ ጠርሙስ ይቀራል?

አስተውሉ፡ እኩል የሆኑ ቁጥሮችን ስናቀናንስ ምንም ቀሪ አይኖርም። በቁጥርም ሲገለፅ 0 ተብሎ ነው።

4.3 ሙሉ ቁጥሮችን በማቀናነስ መፃፍ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የመቀነስ ምልክትን ለይታችሁ ታውቃላችሁ።


ከዚህ በታች የቀረቡትን አስረጂዎች በመጠቀም ቀጥሎ የሚመጡትን መልመጃዎች ሥሩ።

ምሳሌ፡ $20-18=2$፣ $18-16=2$፣ $16-14=2$


በዚህ የተነሳ 2 ከላይ የተገለጹት ሁለት ሙሉ ቁጥሮች በመቀናነሳቸው የመጣ ውጤት ነው።

መልመጃ–3፡


1. ምሳሌውን በማጥናት የሚከተሉትን ባዶ ሳጥኖች ሙሉ።



ሀ.



ሐ.



4.4 ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች


- ከትልቁ ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ትንሹን ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ትቀንሳላችሁ፡፡

ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥርን ከሚበልጠው ወይም እኩል ከሆነው ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር በተለያዩ ዘዴ መቀነስ ይቻላል፡፡


4.4.1 በመቁጠር መቀነስ

በመቁጠር መቀነስ ማለት ከአንድ ስብስብ ውስጥ ተቀናሹን በማስቀረት ወይም በማስወገድ የተቀረውን የስብስብን አባል መቁጠር ማለት ነው፡፡

ምሳሌ *ሀ*)



ምሳሌ *ለ*)



1. ቀጥሎ የተሰጡትን ምስሎች በመመልከት በምሳሌው መሠረት ቀንሱ።

ምሳሌ



5 – 3 = 2

ሀ)



7 – 6 = _____

ለ)



4 – 2 = _____

ሐ)



6 – 1 = _____

መ)



9 – 5 = _____

2. ክፍት ቦታዎችን በትክክለኛው ቁጥር ሙሉ።

$6-5=$ ___	$9-5=$ ___
$6-6=$ ___	$8-3=$ ___
$7-2=$ ___	$9-9=$ ___

3. አስሉ፡፡

$\begin{array}{r} 3 \\ -2 \\ \hline 1 \end{array}$	$\begin{array}{r} 6 \\ -4 \\ \hline 2 \end{array}$	$\begin{array}{r} 7 \\ -5 \end{array}$	$\begin{array}{r} 3 \\ -3 \end{array}$	$\begin{array}{r} 9 \\ -6 \end{array}$	$\begin{array}{r} 8 \\ -7 \end{array}$
$\begin{array}{r} 5 \\ -5 \end{array}$	$\begin{array}{r} 4 \\ -3 \end{array}$	$\begin{array}{r} 8 \\ -7 \end{array}$	$\begin{array}{r} 6 \\ -2 \end{array}$	$\begin{array}{r} 8 \\ -5 \end{array}$	$\begin{array}{r} 1 \\ -1 \end{array}$

4.4.2 የቁጥር መስመር በመጠቀም መቀነስ


ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከሚበልጠው ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንዲሁም ባለ አንድ ሆሄን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር የቁጥር መስመር በመጠቀም መቀነስ ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡

1) $6-1=$ ____

በቁጥር መሥመር ከ6 ላይ 1ን መቀነስ፡፡

መጀመሪያ በቁጥር መሥመር ላይ 6ን አሳዩ፡፡ ቀጥሎ 1 ምድብ ወደ ግራ ሂዱ፡፡ የደረሳችሁበት ቁጥር ልዩነት ይሆናል፡፡




ስለዚህ $6-1=5$ ይሆናል፡፡

መልመጃ-4፡


1) የቁጥር መስመር በመጠቀም የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡

ሀ)




$8 - 2 = \square$

ለ)




$4 - 3 = \square$

ሐ)



$9 - 6 = \square$

መ)



$7 - 3 = \square$

4.5 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን መቀነስ

መግቢያ፡ ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በተለያዩ ዘዴዎች መቀነስ ይቻላል። እነዚህን ዘዴዎች ምሳሌ በመውሰድ እንይ።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ20 የሚያንሱ ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ያለብድር ትቀንሳላችሁ።

ምሳሌ፡

1. $15 - 4 = 10 + 5 - 4$
   $= 10 + 1 = 11$

3) $16 - 12 = 6 - 2$
   $= 4$

2. $14 - 3 = 10 + 4 - 3$
$= 10 + 1 = 11$

መልመጃ−5

1) ከዚህ በላይ ያለውን ምሳሌ በመከተል ቀጥሎ ያሉትን ቀንሱ።

ሀ)	$14 - 4 =$ _____	ሠ)	$13 - 7 =$ _____
ለ)	$18 - 1 =$ _____	ረ)	$14 - 5 =$ _____
ሐ)	$17 - 12 =$ _____	ሰ)	$16 - 11 =$ _____
መ)	$20 - 11 =$ _____	ሸ)	$15 - 14 =$ _____

4.6 የመደመርና የመቀነስ ዝምድና

መግቢያ፡ የመደመርን ውጤት በመቀነስ የመቀነስን ውጤት በመደመር ማረጋገጥ ይቻላል።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በመደመርና በመቀነስ መካከል ያለዉን ዝምድና ትረዳላችሁ።

ምሳሌ፡

ሀ) $13 + 4 = 17$ ምክንያቱም $17 - 4 = 13$ ስለሆነ ነው።

ለ) $3 + 9 = 12$ ምክንያቱም $12 - 9 = 3$ ስለሆነ ነው።


ሐ) $12 - 10 = 2$ ምክንያቱም $2 + 10 = 12$ ስለሆነ ነው።

መ) $\square + 14 = 19$ ምክንያቱም $19 - 14 = \square$

ሠ) $\square - 3 = 10$ ምክንያቱም $10 + 3 = \square$


መልመጃ-6፡ መደመርን ከመቀነስ ጋር በማዛመድ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ባዶ ቦታዎች አሚሉ።

ምሳሌ




$4 + 5 = 9$
$5 + 4 = 9$
$9 - 4 = 5$
$9 - 5 = 4$

ሀ)




□ + □ = □
□ + □ = □
□ - □ = □
□ - □ = □

ሐ)




□ + □ = □
□ + □ = □
□ - □ = □
□ - □ = □

ለ)



□ + □ = □
□ + □ = □
□ - □ = □
□ - □ = □

መ)



□ + □ = □
□ + □ = □
□ - □ = □
□ - □ = □

4.7 የቃላት ፕሮብሌሞች

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- መደመርንና መቀነስን ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትሰራላችሁ፡፡

1) እማማ 10 አበባዎች ነበሯት ከአስር አበባዎች ውስጥ የተወሰኑትን ባልዲ ውስጥ አስቀምጣ ሦስት አበባዎች ቀሯት፡፡ እማማ ስንት አበባዎችን ባልዲ ውስጥ አስቀመጠች?

2) በአንድ ቦርሳ ውስጥ 3 እርሳሶች ነበሩ፡፡ ከቦርሳው ውስጥ በላይነሽ ፣ተሰማ እና መሐመድ አንዳንድ እርሳስ ቢወስዱ ቦርሳ ውስጥ ስንት እርሳስ ይቀራል?

3) በቤታችሁ ውስጥ 15 በጎች አሉ፡፡ 3 በጎች ተሸጡ፡፡ በቤት ውስጥ የቀሩት በጎች ስንት ናቸው?

4) አቶ አለማየሁ በኪሱ 18 ብር ነበረው፡፡ ለአቶ ክንፈ 7ብር ቢሰጠው አለማየሁ በኪሱ የቀረው ብር ምን ያህል ነው?

5) አንድ ተማሪ ከአባቱ 20ብር ለደብተር እና እስክሪብቶ መግዣ ተሰጠው፡፡ በ6ብር እስክሪብቶ ቢገዛ በኪሱ ስንት ብር ይቀራል?

የማጠቃለያ መልመጃ

1. ባዶ ቦታውን በትክክለኛው ቁጥር ሙሉ


8 −2	14 −3	6 −2	7 −6	5 −4	19 −3

2. አስሉ

ሀ)	$7-1=$ _____	መ)	$15-1=$ _____
ለ)	$9-5=$ _____	ሠ)	$8-0=$ _____
ሐ)	$12-2=$ _____	ረ)	$7-2=$ _____


3. የቁጥር መስመሩን በመጠቀም የባዶ ቦታውን ዋጋ ፈልጉ።

ሀ)




$6-3=$ _____

ለ)



$17-11=$ _____

ሐ)



$9-2=$ _____

4. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

ሀ) ሁለት እንቁላሎች በሰሀን ላይ ተቀምጠዋል። ሁለቱ ወድቀው ሲሰበሩ በሰሀኑ ላይ ስንት እንቁላሎች ይቀራሉ?

ለ) ለማ 3 እርሳሶች ነበሩት።አንድ እርሳስ ቢጠፋበት የሚቀሩት እርሳሶች ስንት ናቸው?

ሐ) በዚህ አመት ትምህርት ቤታችን ሲከፈት 9 ያልተፃፈባቸው አዲስ ደብተሮች ነበሩኝ። ትምህርት ሲጀመር በሁሉም ደብተሮቼ መፃፍ ጀመርኩ። አሁን ስንት ያልተፃፈባቸው አዲስ ደብተሮች አሉኝ ማለት ነው?

ምዕራፍ-5

እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

መግቢያ፡ ባለፈው ምዕራፍ እስከ 20 ያሉትን ሙሉ ቁጥሮች ተምረናል።

እነዚህም ቁጥሮች በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው።

0 1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

11 12 13 14 15 16 17 18 19 20

አሁን ደግሞ በዚህ ምዕራፍ እስከ 100 ድረስ ያሉትን ሙሉ ቁጥሮች እንማራለን።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በተለየ መንገድ ከ1 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ።
- የቁጥሮችን አንፃራዊ መጠንና ዋጋ ይረዳሉ።

5.1 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 10 ምድብ መቁጠር






መግቢያ፡ በዚህ ርዕስ እስከ 100 ያሉትን የአስር ብዜት ቁጥሮች መቁጠር፣ ማንበብ እና መጻፍን እንማራለን።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የአስር ብዜት የሆኑ ቁጥሮችን ትቆጥራላችሁ።

የሚከተሉትን አጥኑ

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■	10

	10 + 10
	10 + 10 + 10
	10 + 10 + 10 + 10
	10 + 10 + 10 + 10 + 10
	10 + 10 + 10 + 10 + 10 + 10

$10 = 10$	አሥር
$10 + 10 = 20$	ሃያ
$20 + 10 = 30$	ሰላሣ
$30 + 10 = 40$	አርባ
$40 + 10 = 50$	ሃምሣ
$50 + 10 = 60$	ስልሳ

የቡድን ሥራ-1

1. አንብቡ

10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
አሥር	ሃያ	ሠላሳ	አርባ	ሃምሳ	ስልሳ	ሰባ	ሰማንያ	ዘጠና	መቶ

2. በየደብተራችሁ ላይ ደጋግማችሁ ጻፉ።

10								
20								
30								
40								
50								
60								

70								
80								
90								
100								

አስተውሉ፡ 10፣ 20፣ 30፣ 40፣ 50፣ 60፣ 70፣ 80፣ 90፣ 100 የአሥር ምድቦች ናቸው።።

መልመጃ–1፡

1) በምሳሌው መሠረት ባዶ ቦታውን ሙሉ።።

1 አሥር = 10	6 አሥሮች = _____
2 አሥሮች = 20	7 አሥሮች = _____
3 አሥሮች = _____	8 አሥሮች = _____
4 አሥሮች = _____	9 አሥሮች = _____
5 አሥሮች = _____	10 አሥሮች = _____

30 = 3 አሥሮች	90 = _____
70 = 7 አሥሮች	100 = _____
40 = _____	80 = _____
60 = _____	50 = _____

10 = _____	**20 = _____**

2) በምሳሌው መሠረት ደምሩ።

$2+3=5$ **ከሆነ** $20+30=50$
$1+2=3$ **ከሆነ** $10+20=$ _____
$3+3=6$ **ከሆነ** $30+30=$ _____
$4+2=6$ **ከሆነ** $40+20=$ _____
$5+4=9$ **ከሆነ** $50+40=$ _____
$2+5=7$ **ከሆነ** $20+50=$ _____

3) ቀንሱ

$4-3=1$ **ከሆነ** $40-30=10$
$5-1=4$ **ከሆነ** $50-10=$ _____
$3-2=1$ **ከሆነ** $30-20=$ _____
$5-4=1$ **ከሆነ** $50-40=$ _____
$7-5=2$ **ከሆነ** $70-50=$ _____
$8-4=4$ **ከሆነ** $80-40=$ _____
$9-5=4$ **ከሆነ** $90-50=$ _____

5.2 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር

መግቢያ፡ በቀደመው ርዕስ እስከ 100 ያሉትን የ10 ብዜቶችን አጥንታችኋል።

እነዚህም ቁጥሮች በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው።

10 ፣ 20 ፣ 30 ፣ 40 ፣ 50 ፣ 60 ፣ 70 ፣ 80 ፣ 90 ፣ 100



አሁን ደግሞ ከ20 እስከ 100 ያሉትን የ10 ብዜት ያልሆኑትን ሙሉ ቁጥሮች ጨምራችሁ ትማራላችሁ።


ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በቃል ትቆጥራላችሁ።
- ከ 20 አስከ 100 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን በሆሄና በፊደል ታነባላችሁ ትፅፋላችሁ።

ተግባር-1



በምሳሌው መሠረት ባዶ ቦታውን ሁለት ሁለት በመሆን እየተወያያችሁ ሙሉ።



ምሳሌ 	___አሥር እና ___አንዶች 1 አሥር እና 4 አንዶች
	___አሥሮች እና-----አንዶች


	_____አሥር እና _____አንድ

መልመጃ–2፡

1. በባዶ ቦታው የምስሎቹን ብዛት ቁጥራችሁ በምሳሌው መሠረት ሙሉ።

ምሳሌ	
	
_____አሥሮች እና_____አንዶች 2 አሥሮች እና 8 አንዶች	_____አሥሮች እና____አንዶች 2 አሥሮች እና 3 አንዶች

ሀ.		ለ.	

			
	---------አሥሮች እና---- -----አንዶች		---------አሥሮች እና---------አንዶች

2. አንብቡ

ሃያ አንድ	21	ሃያ ስድስት	26
ሃያ ሁለት	22	ሃያ ሰባት	27
ሃያ ሦስት	23	ሃያ ስምንት	28
ሃያ አራት	24	ሃያ ዘጠኝ	29

ሃያ አምስት	25	ሠላሳ	30
ሠላሳ አንድ	31	ሠላሳ ስድስት	36
ሠላሳ ሁለት	32	ሠላሳ ሰባት	37
ሠላሳ ሦስት	33	ሠላሳ ስምንት	38
ሠላሳ አራት	34	ሠላሳ ዘጠኝ	39
ሠላሳ አምስት	35	አርባ	40
አርባ አንድ	41	አርባ ሰባት	47
ሃምሳ ዘጠኝ	59	አርባ ሁለት	42
ስልሳ ስድስት	66	አርባ ዘጠኝ	49
ዘጠና ሁለት	92	ሃምሳ ሦስት	53
ዘጠና ስድስት	96	ሰማንያ አንድ	81
ስልሳ ሁለት	62	ሰባ አራት	74
ሰማንያ ዘጠኝ	89	ዘጠና ሰባት	97
ሃምሳ ሰባት	57	ሰባ አምስት	75

3. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፍ/ፊ።

ሀ) ሰላሳ ሦስት = ____ ለ) ሰባ አንድ = ____

ሐ) ሃምሳ አንድ =_____ መ) አርባ ስድስት=_____

ሠ) አስራ ሁለት=_____

4. በምሳሌው መሠረት ባዶ ቦታውን ሙሉ።

አሥራ ሁለት ⟶ 12 ሃያ ስድስት ⟶ 26	45 ⟶ አርባ አምስት 91 ⟶ ዘጠና አንድ
ሠላሳ አንድ ⟶ _____ አርባ ዘጠኝ ⟶ _____	41 ⟶ _____ 52 ⟶ _____
ስልሳ ሁለት ⟶ _____ ሰባ አራት ⟶ _____	94 ⟶ _____ 87 ⟶ _____
ሰማንያ አራት ⟶ _____ አርባ ሦስት ⟶ _____	93 ⟶ _____ 88 ⟶ _____
ዘጠና ሰባት ⟶ _____ ሃምሳ ሁለት ⟶ _____	26 ⟶ _____ 33 ⟶ _____
አርባ ዘጠኝ ⟶ _____ ሰላሳ ስድስት ⟶ _____	48 ⟶ _____ 56 ⟶ _____
ሰባ ሰባት ⟶ _____ ሃምሳ አምስት ⟶ _____	28 ⟶ _____ 97 ⟶ _____

5. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች በፍደል ፃፍ/ፊ።

ሀ) 37 = _____ ለ) 69 = _____

ሐ) 83 = _____ መ) 53 = _____

ሠ) 73 = _____

5.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 100 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን ታነባፅራላችሁ፡፡
- አስከ 100 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተሎቻቸዉ መሰረት ትደረድራላችሁ፡፡
- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በመረዳት አንባራዊ ቦታቸውና መጠናቸውን ትገልፃላችሁ፡፡

ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ ጎንና ቁልቁል አንብቡ፡፡

1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
11	12	13	14	15	16	17	18	19	20
21	22	23	24	25	26	27	28	29	30
31	32	33	34	35	36	37	38	39	40
41	42	43	44	45	46	47	48	49	50
51	52	53	54	55	56	57	58	59	60
61	62	63	64	65	66	67	68	69	70
71	72	73	74	75	76	77	78	79	80
81	82	83	84	85	86	87	88	89	90
91	92	93	94	95	96	97	98	99	100

መልመጃ-3፡

1) በምሳሌው መሠረት > ወይም < ምልክት በመጠቀም ክፍት ቦታውን ሙሉ።

ሀ.

5 > 2 ስለሆነ 50 > 20
4___3 ስለሆነ 40___30
7___1 ስለሆነ 70__10
8__ 4 ስለሆነ 80__40
9__5 ስለሆነ 90__50

ለ.

6 < 9	61 < 91
3___6	32___62
4___5	49__59
7__ 8	77__87
6__7	63__ 73

2) በምሳሌው መሠረት በትክክለኛው ምልክት ክፍት ቦታውን ሙሉ።

ሀ.

5 < 6	54_____60
3 < 7	39_____70
4 < 5	41_____50
6_____2	60_____28
7_____5	70_____56
8_____4	80_____44

ለ.

6_____7	67_____74
4_____5	43_____51
2_____4	29_____46

5_____1	50_____19
6_____2	66_____28
4_____3	44_____36
7_____9	74_____92

3) የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ቁጥር በመጀመር በቅደም ተከተል ዘርዝሩ።

ሀ. 36፣ 42፣ 18፣ 24 እና 57

ለ. 83፣ 60፣ 29፣ 42፣ እና 64


ሐ. 30፣ 20፣ 60፣ 80 እና 22

4) ክፍት ቦታዎችን ሙሉ።


ሀ.	2፣ 4፣ 6፣____ 10፣ 12፣____ ፣____፣____ ፣ 20 ::
ለ.	10፣ 20፣ ____ ፣ ____፣ 50 ፣ ____ ፣ ____ ፣____ ፣90 ::
ሐ.	20፣18፣16፣____፣ ____፣ ____፣ ____፣ ____፣ ____፣ 2 ::
መ.	5፣ 10፣ 15፣ 20፣ ____፣ ____፣ ____፣ ____፣ 45 ::
ሠ.	100፣ 90፣ 80፣ ____፣____፣____፣____፣____፣____10 ::

5) ባዶ ሳጥኖችን በትክክለኛው ቁጥሮች ሙሉ።

ሀ.



ለ.



ሐ.



6) በተሰጡት ሁለት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙትን ሙሉ ቁጥሮች በዝርዝር ጻፉ።

ሀ) በ 3 እና በ 9 ለ) በ 30 እና በ 40

ሐ) በ 15 እና በ 25 መ) በ 84 እና በ 90

7) ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ።

31 12 57 26 19 73 85

8) ከ10 እስከ 30 ያሉትን ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ጨረር ወይም በቁጥር መስመር ላይ በቅደም ተከተላቸው አሳዩ።

5.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን የአንድና የአስር ቤት ዋጋ ትናገራላችሁ።

ቀደም ብለን እንዳየነው ለምሳሌ 25 ማለት $20+5$ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሁለት አስሮች እና 5 አንዶች ማለት ነው።

ስለዚህ የ25 የአሥር ቤት ዋጋ 2 ሲሆን የአንድ ቤት ዋጋው 5 ነው። በዚህ

መሠረት የ25ን የቁጥር ቤት ዋጋ በሚከተለው መልክ መግለጽ ይቻላል፡፡



የሌሎቹንም ቁጥሮች የቤት ዋጋ በዚሁ ዓይነት መግለጽ ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡

የተሰጠው ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
52	5	2
36	3	6
48	4	8

በዚህ ምሳሌ የተገለጹትን ቁጥሮች በሚከተለው ሁኔታ የዋጋ ቤታቸውን መግለጽ ይቻላል፡፡

$52 = 50 + 2$ (5 አሥሮች እና 2 አንዶች)

$36 = 30 + 6$ (3 አሥሮች እና 6 አንዶች)

$48 = 40 + 8$ (4 አሥሮች እና 8 አንዶች)

መልመጃ-4፡

1. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሙሉ ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
18	1	8
24	2	4
80	8	0
31		
46		
85		
93		

2. ከዚህ በታች ያሉት ቁጥሮች ስንት አሥሮች እና ስንት አንዶች እንዳሏቸው ግለፅ/ጪ።

ምሳሌ፡- 65 = 60 + 5 በዚህ ቁጥር ላይ 6 አሥሮች እና 5 አንዶች አሉ።

ሀ) 42 = _____ አሥሮች እና _____ አንዶች አሉት።

ለ) 36 = _____ አሥሮች እና _____ አንዶች አሉት።

ሐ) 67 = _____ አሥሮች እና _____ አንዶች አሉት።

መ) 85 = _____ አሥሮች እና _____ አንዶች አሉት።

ሠ) 78 = _____ አሥሮች እና _____ አንዶች አሉት።

3. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፏቸው።

ሀ) 5 አሥሮች እና 9 አንዶች = _____።

ለ) 8 አሥሮች እና 5 አንዶች = _____።

ሐ) 4 አሥሮች እና 0 አንዶች = _____።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. ቀጥለዉ ለተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይ እና ተከታይ ፈልጉ።

ሀ) የ 10 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

ለ) የ 30 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

ሐ) የ 51 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

መ) የ 75 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

ሠ) የ 99 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነዉ።

2. ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ) 20፣25፣30፣____፣____ ፣____ ፣____ ፣55 ::

ለ) 10፣20፣30፣____፣____ ፣____፣____ ፣____፣____ ፣100::

ሐ) 15፣25፣____፣____፣____ ፣____፣____ ፣____፣95።

3. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩን አግኙ።

ሀ) 26 ለ) 35 ሐ) 50 መ) 66 ሠ) 84

4. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ተከታይ ሙሉ ቁጥሩን አግኙ።

ሀ) 21 ለ) 32 ሐ) 37 መ) 55 ሠ) 99

5. በተሰጡት ሁለት ቁጥሮች መካከል ያሉትን ሙሉ ቁጥሮች አንድ በአንድ በቅደም ተከተል ዘርዝሩ።

ሀ) 25 እና 32 ለ) 81 እና 95

ሐ) 65 እና 75 መ) 8 እና 17

6. ከተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀጥሎ ያሉትን አምስት አምስት ሙሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ዘርዝሩ።

ሀ) 10 ለ) 20 ሐ) 40 መ) 50

7. የሚከተሉትን ቁጥሮች ስርዓት ተገንዝባችሁ በሥርዓቱ መሠረት የቀሩትን ሙሉ ቁጥሮች በባዶ ቦታዉ ሙሉ።

ምሳሌ:- 5፣10፣15፣20፣25፣30፣35፣40፣45

ሀ) 18፣16፣___፣___10፣___፣___፣4።

ለ) 78፣79፣___፣___፣82፣___፣___፣___።

ሐ) 99፣96፣93፣___፣87፣___፣___።

8. የቁጥሮችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የጎደለውን ቁጥር ሙሉ

ምሳሌ	61		63	64	___61	___62	___63	___64
ሀ)		44	45	46	____	____	____	____
ለ)	90			93	____	____	____	____
ሐ)		56	57		____	____	____	____

9. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፏቸው።

ሀ) 5 አስሮች እና 9 አንዶች = _____።

ለ) 8 አስሮች እና 5 አንዶች = _____።

ሐ) 4 አስሮች እና 0 አንዶች = _____።

መ) 6 አስሮች እና 6 አንዶች = _____።

10. በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ የ 4 የቁጥርን ቤት ዋጋን ሰይሙ።

ሀ) 84 ለ) 74 ሐ) 46 መ) 40 ሠ) 48

ምዕራፍ-6

እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

መግቢያ፡ እስከ 100 ካሉ ሙሉ ቁጥሮች መካከል ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር እንዲሁም ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም መደመር እና መቀነስ ይቻላል። በዚህ ምዕራፍ እነዚህን ዘዴዎች እንመለከታለን።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ድምራቸዉ ከ100 የማይበልጡ ሁለት ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ።
- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ወይም ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከሚበልጠዉ ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ይቀንሳሉ።
- ቁጥሮችን የመነጣጠልና የመገጣጠም ፅንሰ ሀሳብን በመጠቀም ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ ትቀንሳላችሁ።

6.1 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር መደመር

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር ትደምራላችሁ።

መግቢያ፡ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር የመነጣጠል እና የመገጣጠም ዘዴን በመጠቀም መደመር ይቻላል። እነዚህን ዘዴዎች ምሳሌ በመውሰድ እንይ።

ምሳሌ፡-

1. $15 + 4 = 10 + 5 + 4$
$= 10 + 9$
$= 19$

2. $26 + 2 = 20 + 6 + 2$
$= 20 + 8$
$= 28$

3. $62 + 5 = 60 + 2 + 5$
$= 60 + 7$
$= 67$

4. $94 + 3 = 90 + 4 + 3$
$= 90 + 7$
$= 97$

መልመጃ 1

ከዚህ በላይ ያለውን ምሳሌ በመከተል ቀጥሎ ያሉትን ደምር/ሪ።

ሀ) $14 + 3 =$ ___ መ) $66 + 2 =$ ___ ሰ) $82 + 7 =$ ___

ለ) $35 + 3 =$ ___ ሠ) $94 + 3 =$ ___ ሸ) $73 + 6 =$ ___

ሐ) $23 + 7 =$ ___ ረ) $44 + 2 =$ ___ ቀ) $54 + 5 =$ ___

ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓትን በመጠቀም መደመር ይቻላል ይህንንም ምሳሌ በመዉሰድ እንመልከት።

ምሳሌ፡-የቁጥር ቤትን በመጠቀም ደምሩ።

ሀ) $15 + 2$ ለ) $23 + 5$ ሐ) $64 + 1$

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
1	5
+	2
1	7

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
2	3
+	5
2	8

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
6	4
+	1
6	5

መልመጃ -2

ከላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመከተል ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች ደምሩ ።

ሀ) $17 + 2 =$ _____ ለ) $23 + 4 =$ _____ ሐ) $34 + 2 =$ _____

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
1	7
+	2

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
2	3
+	4

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
3	4
+	2

6.2 ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄያት ቁጥርን መቀነስ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡ -

- ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄያት ቁጥሮችን ትቀንሳላችሁ።

መግቢያ፡- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በመነጣጠልና በመገጣጠም እንዲሁም የቁጥር ቤት ሥርዐትን በመጠቀም መቀነስ ይቻላል።

ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ለመቀነስ የመነጣጠልና የመገጣጠም ዘዴን መጠቀም እንችላለን።

ምሳሌ፡-

ሀ) $15 - 4 = 10 + 5 - 4$
$= 10 + 1$
$= 11$

ለ) $28 - 7 = 20 + 8 - 7$
$= 20 + 1$
$= 21$

ሐ) $39 - 5 = 30 + 9 - 5$

$= 30 + 4$

$= 34$

መልመጃ -3

ከላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመከተል ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች ቀንሱ።

ሀ) $16 - 3 =$ ___ ለ) $49 - 2 =$ ___ ሐ) $28 - 4 =$ ___

መ) $64 - 3 =$ __ ሠ) $88 - 6 =$ __ ረ) $35 - 1 =$___

ሰ) $76 - 4 =$ __ ሸ) $97 - 5 =$ __ ቀ) $57 - 5 =$ __

ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ እንድ ሆሄ ቁጥርን ለመቀነስ የቁጥር ቤት ሥርዓትን መጠቀም እንችላለን።

ምሳሌ፦ የሚከተሉትን የቁጥር ቤት ሥረዓትን በመጠቀም ቀንሱ።

ሀ) $36 - 4 =$ ___

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
3 –	6 4
3	2

መጀመሪያ ከ 6 ላይ 4ን ቀንሱ። 2 ታገኛላችሁ። 2ን በአንድ ቤት ሥር ፃፉ። 3 ን በቀጥታ አውርዳችሁ በአሥር ቤት ሥር ፃፉ። ከዚህ የተነሳ $36 - 4 = 32$ ይሆናል።

ለ) $76 - 5 = ___$

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
7 –	6 5
7	1

መጀመሪያ ከ 6 ላይ 5ን ቀንሱ። 1 ታገኛላችሁ። 1ን በአንድ ቤት ሥር ፃፉ። 7ን ደግሞ በአሥር ቤት ስር ፃፉ።ከዚህ የተነሳ $76 - 5 = 71$ ይሆናል።

መልመጃ -4

1. በምሳሌው መሠረት ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች ቀንሱ።

ሀ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
1 –	7 4

ለ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
2 –	6 3

ሐ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
3 –	6 4

መ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
4 –	5 2

ሠ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
6 –	5 2

ረ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
1 –	7 4

ሰ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
7	9
−	5

ሸ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
8	7
−	3

ቀ)

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
7	6
−	3

2. ከዚህ በታች ያሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች መልስ/ሺ፡፡

ሀ) አቶ ከበደ ባለፈው ዓመት 12 የወይራ ችግኞችን ተክለው ነበር በዚህ ዓመት ደግሞ 2 የወይራ ችግኞችን ተከሉ፡፡ አቶ ከበደ በአጠቃላይ ስንት ችግኞችን ተከሉ?

ለ) አልማዝ 46 ብር አላት፡፡ በ 5 ብር ሙዝ ብትገዛ ስንት ብር ይቀራታል?

ሐ) አቶ ቶማስ በ 85 ብር ደብተር እና በ 4 ብር እርሳስ ገዙ፡፡ አቶ ቶማስ በአጠቃላይ ስንት ብር አወጡ?

መ) ትዕግስት 18 ብርቱኳኖች አሏት፡፡ 3 ብርቱኳኖችን ብትበላ እና 2ቱን ደግሞ ለእህቷ ብትሰጥ ስንት ብርቱኳኖች ይቀሯታል?

6.3 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን መደመር

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡ -

- ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ጋርትደምራላችሁ፡፡

መግቢያ፡ ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ጋር በመነጣጠልና በመገጣጠም መደመር ይቻላል፡፡ መጀመሪያ የአንድ ቤትን ከአንድ ቤት ጋር በመደመር፡፡ በመቀጠል የአሥር ቤትን ከአሥር ቤት ጋር በመደመር ውጤቱን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡

ሀ) $12 + 16 = 10 + 2 + 10 + 6$

$= 10 + 10 + 2 + 6$

$= 20 + 8$

$= 28$

ለ) $24 + 13 = 20 + 4 + 10 + 3$

$= 20 + 10 + 4 + 3$

$= 30 + 7$

$= 37$

መልመጃ -5

1. ከዚህ በታች ያሉትን ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ደምሩ፡፡

ሀ) $15 + 14 =$ _____ ለ) $14 + 11 =$ _____ ሐ) $81 + 15 =$ _____

መ) $72 + 24 =$ _____ ሠ) $43 + 56 =$ _____ ረ) $25 + 32 =$ _____

ሰ) $20 + 19 =$ _____ ሸ) $38 + 41 =$ _____ ቀ) $13 + 22 =$ _____

ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮች ጋር የቁጥር ቤት ዋጋ ፅንሰ ሀሳብን በመጠቀም ያለአለኝታ መደመር ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡-

1. ደምር/ሪ

$35 + 24 =$ _____

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
3	5
+ 2	4
5	9

መጀመሪያ የአንድ ቤትን ደምሩ።

$5 + 4 = 9$

በመቀጠል የአስር ቤትን ደምሩ።

$3 + 2 = 5$ ስለዚህ $35 + 24 = 59$

2. ደምር/ሪ

$21 + 46 =$ _____

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
2	1
+ 4	6
6	7

መጀመሪያ የአንድ ቤትን ደምሩ።

$1 + 6 = 7$

በመቀጠል የአስር ቤትን ደምሩ።

$2 + 4 = 6$ ስለዚህ $21 + 46 = 67$

መልመጃ-6

1. ከዚህ በታች ያሉትን ደምር/ሪ

ሀ) $\begin{array}{r} 45 \\ +\ 33 \\ \hline \end{array}$ ለ) $\begin{array}{r} 53 \\ +\ 26 \\ \hline \end{array}$ ሐ) $\begin{array}{r} 38 \\ +\ 41 \\ \hline \end{array}$

መ) $\begin{array}{r} 43 \\ +\ 56 \\ \hline \end{array}$ ሠ) $\begin{array}{r} 84 \\ +\ 13 \\ \hline \end{array}$ ረ) $\begin{array}{r} 63 \\ +15 \\ \hline \end{array}$


ሰ) $\begin{array}{r} 72 \\ +\ 25 \\ \hline \end{array}$ ሸ) $\begin{array}{r} 68 \\ +\ 11 \\ \hline \end{array}$ ቀ) $\begin{array}{r} 80 \\ +10 \\ \hline \end{array}$

በ) 25 + 14 ተ) 75 + 21 ቸ) 38 +41


ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓትን በመጠቀም በአለኽታ መደመር እንችላለን፡፡

ምሳሌ፡ -

ሀ) 46 + 38 = ____



ለ) 53 + 29 = ____



መልመጃ-7

ከዚህ በታች ያሉትን በምሳሌው መሠረት ደምሩ።

ሀ) 46 + 17

ለ) 65 + 28

ሐ) 69 + 28

መ) 73 + 19

ሠ) 27 + 23

ረ) 67 + 13

ሰ) 56 + 27

ሸ) 58 + 27

ቀ) 37 + 29

6.4 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን መቀነስ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡ -

- ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ትቀንሳላችሁ።

መግቢያ፡- ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ለመቀነስ የቁጥር ቤት ሥርዓትን፣ የመነጣጠልና የመጋጠም ጽንሰ ሀሳብን እንጠቀማለን።

ይህን ዘዴ ለማለማመድ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡:

ምሳሌ፡-

ሀ) $28 - 17 = 20 - 10 + 8 - 7$
$= 10 + 1$
$= 11$

ለ) $78 - 15 = 70 - 10 + 8 - 5$
$= 60 + 3$
$= 63$

መልመጃ -8

ከዚህ በላይ በተሰጠዉ ምሳሌ መሠረት ደምሩ።።

ሀ) $36 - 27 =$ ___ **ለ)** $47 - 36 =$ ___ **ሐ)** $56 - 34 =$ ___

መ) $77 - 14 =$ ___ **ሠ)** $63 - 19 =$ ____ **ረ)** $76 - 3 =$ __

ሰ) $76 - 28 =$ __ **ሸ)** $88 - 6 =$ ___ **ቀ)** $89 - 29 =$ __

ምሳሌ፡-

የሚከተሉትን የቁጥር ቤት ሥረዓትን በመጠቀም ቀንሱ

1. $46 - 32 =$ ___

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
4	6
− 3	2
1	4

መጀመሪያ የአንድ ቤትን ቀንሱ።።

$6 - 2 = 4$

በመቀጠል የአሥር ቤትን ቀንሱ።።

$4 - 3 = 1$ **ስለዚህ** $46 - 32 = 14$

2. $87 - 43 = ___$

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
8	7
- 4	3
4	4

መጀመሪያ የአንድ ቤትን ቀንሱ፡፡

$7 - 3 = 4$

በመቀጠል የአሥር ቤትን ቀንሱ፡፡

$8 - 4 = 41$ **ስለዚህ** $87 - 43 = 44$

መልመጃ -9

1. ከዚህ በታች ያሉትን ቀንስ/ሺ፡፡

ሀ) $\begin{array}{r} 25 \\ -\,14 \\ \hline \end{array}$ ለ) $\begin{array}{r} 36 \\ -\,24 \\ \hline \end{array}$ ሐ) $\begin{array}{r} 43 \\ -32 \\ \hline \end{array}$

መ) $\begin{array}{r} 58 \\ -23 \\ \hline \end{array}$ ሠ) $\begin{array}{r} 49 \\ -13 \\ \hline \end{array}$ ረ) $\begin{array}{r} 63 \\ -42 \\ \hline \end{array}$

ሰ) $\begin{array}{r} 68 \\ -55 \\ \hline \end{array}$ ሸ) $\begin{array}{r} 76 \\ -\,56 \\ \hline \end{array}$ ቀ) $\begin{array}{r} 73 \\ -12 \\ \hline \end{array}$

በ) $\begin{array}{r} 83 \\ -72 \\ \hline \end{array}$ ተ) $\begin{array}{r} 86 \\ -\,63 \\ \hline \end{array}$ ቸ) $\begin{array}{r} 45 \\ -14 \\ \hline \end{array}$

6.5 የቃላት ፕሮብሌሞችን መደመርና መቀነስን በመጠቀም ማስላት

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡ -

- ድምራቸው ወይም የመቀነስ ውጤታቸዉ ከ 100 የማይበልጡ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ

ከዚህ በታች እስከ 100 ላሉ ቁጥሮች በውስጡ መደመርንና እና መቀነስን የያዘ የቃላት ፕሮብሌሞችን እንመለከታለን፡፡

ምሳሌ፡- ከዚህ በታች የተሰጡትን የቃላት ፕሮብሌሞችን ሥሩ፡፡

ሀ) ከድር 46 ፍየሎች ነበሩት፡፡ 12 ፍየሎችን ቢሸጥ ስንት ፍየሎች ይቀሩታል?

መልስ ፡ ከነበሩት የፍየሎች ብዛት ላይ የሸጠውን ስንቀንስ የሚቀሩትን የፍየሎች ብዛት ማወቅ ይቻላል፡፡

ይህ ማለት $46 - 12 = 40 - 10 + 6 - 2 = 30 + 4 = 34$ ፍሎች ይቀሩታል፡፡

ለ) ፎዚያ 36 ብርቱካኖች አሏት፡፡ 22 ብርቱካኖችን ተጨማሪ ብትገዛ ፎዚያ በአጠቃላይ ስንት ብርቱካኖች ይኖሯታል፡፡

መልስ ፡ ፎዚያ የሚኖራትን የብረትካን መጠን ለማወቅ መጀመሪያ በነበራት የብርቱካን ብዛት ላይ በተጨማሪ የገዛችውን እንደምራለን፡፡

ይህ ማለት $36 + 22 = 30 + 6 + 20 + 2 = 30 + 20 + 6 + 2 = 50 + 8 = 58$

መልመጃ-10

ከዚህ በታች ያሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች መልስ/ሺ

1) አቶ በቀለ ለንግድ 76 ብርቱካኖችን ገዙ። ከዚህ ውስጥ 28 ብርቱካኖችን ቢሸጡ ስንት ብርቱካኖች ቀሯቸዋል?
2) ወ/ሮ ጌጤ ስኳር በ65 ብር እና ጨው በ20 ብር ሸጡ። በአጠቃላይ ስኳሩ እና ጨውን በስንት ብር ሸጡ?
3) አብዴላ 63 ብር አለው። 17 ብር አባቱ እና 16 ብር ወንድሙ ጨመሩለት ። በአጠቃላይ አብዴላ ስንት ብር አለው?
4) የሚቀጥለውን ሰንጠረዥ የኩልፎ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ብዛት ያመለክታል።

ክፍል	የተማሪዎች ብዛት
1ኛ	25
2ኛ	37
3ኛ	23
4ኛ	14

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከታችሁት የኩልፎ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

5) ሀብታሙ፣ ሙሉቀን እና ውብሸት የተከሉት የችግኞች ብዛት በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተሰቷል።

ስም	የችግኝ ብዛት
ሀብታሙ	38
ሙሉቀን	47

ውብሸት	29

ሀ) ሀብታሙ እና ሙሉቀን ስንት ችግኞች ተከሉ?

ለ) ሙሉቀን እና ውብሸት በአጠቃላይ የተከሉት ችግኞች ብዛት ስንት ነው?

ሐ) ሀብታሙ እና ውብሸት በአጠቃላይ የተከሉት ችግኞች ብዛት ስንት ነው?

መ) ሙሉቀን የተከለው ችግኝ ሀብታሙ ከተከለው ችግኝ በስንት ይበልጣል?

ሠ) ሀብታሙ የተከለው ችግኝ ውብሸት ከተከለው ችግኝ በስንት ይበልጣል?

ምዕራፍ-7

ቅርፆች

መግቢያ: ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን መለየት እንዲሁም በማንኛውም ጠለል ላይ ምስላቸውን መሳል፣ የታወቁ ባለ ሁለት አውታር ምስሎች የባህሪይ መለያን በራስ ቋንቋ መግለጽን እና በስም መጥራት በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡



የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን ግማሽ ክብ፤ዲያመንድ፤ሞላላ፤አምስት ጎን እና ስድስት ጎንን በስም ትሌላችሁ፡፡
- የባለ ሁለት አዉታር ምስሎች የባህሪ መለያን በራሳችሁ ቋንቋ ትገልፃላችሁ፡፡

የቡድን ሥራ-1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው፤ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ወይም የሰራችሁትን ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ቀጥሎ ያሉትን ምሥሎች ተመልከቱ፡፡ የሚከተሉትንም ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡

ሀ.  ለ.  ሐ. 

ሀ. የሒሳብ መጽሐፋችሁ ቅርፅ ከነዚህ ምስሎች የትኛውን ይመስላል?

ለ. የክፍላችሁ ወለል ጠርዝስ ከየትኛው ምስል ጋር ይመሳሰላል?

ሐ. በመኖሪያችሁ አካባቢ ከነዚህ ምስሎች ጋር የሚመሳሰሉ ነገሮች ካሉ ዘርዝሯቸው።

መ. ወረቀት ወይም ክላሰር በመጠቀም ከላይ ያሉትን ምስሎች አስመስላችሁ ቆርጣችሁ አውጡ።

ሠ. ከላይ የተሰጡትን ምስሎች የማስመሪያ ጠርዝ እንዲሁም የሳንቲም ዲናር ጠርዝ በመጠቀም አስመስላችሁ ሳሉ።

7.1 ባለሁለት አዉታር ምስሎችን መለየት

መግቢያ፡ ባለ ሁለት አውታር ምስሎች ጠለል ላይ መስመሮችን በመጠቀም የሚሳሉ ቅርፆች ሲሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጸዋል።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን በስም ይለያሉ።

ተግባር-1

ከሚከተሉት ምስሎች የትኞቹ ጎነ ሦስት ፣ የትኞቹ ጎነ አራት እና የትኞቹ ደግሞ ክብ እንደሆኑ ለይታችሁ ተናገሩ

ሀ)



ለ)



ሐ)



መ)




ሠ)



ረ)



ሰ)



አስተውሉ፡ ከላይ የተሰጡት ምሥሎች የሚከተሉት ስያሜ አላቸው፡፡

በምስል ሀ የሚታየው ጎነ አራት ይባላል፡፡

በምስል ለ የሚታየው ክብ ይባላል፡፡

በምስል ሐ የሚታየው ጎነ ሦስት ይባላል፡፡

ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች ከነስያሜያቸው ቀርበዋል በትኩረት ተመልከቱ፡፡

ሀ.



ጎነ ሶስት

ለ.



ጎነ አራት

ሐ.



ጎነ አምስት


መ.



ጎነ ስድስት







ሠ.  ክብ



ረ.  ሞላላ

ሰ  ድያመንድ


መልመጃ -1፡


1. በስተግራ ለተገለጹት ስሞች ተመሳሳይ የሆነውን ቅርፆች በማቅለም አሳዩ፡፡

ክብ				
ጎነ አራት				
ግማሽ ክብ				
ድያመንድ				

ኮከብ	
ጎነ ሦስት	
ሞላላ	

2. ተመሳሳይ ምስሎች ማዛመድ












7.2 ባለሁለት አውታር ምስሎችን መሳል

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች


- ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን በስም ይለያሉ።

የሚከተሉትን ምስሎች በምሳሌዉ መሠረት በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ደጋግማችሁ ሳሉ

ምሳሌ፡ 	  


ተግባር-2 የሚከተለትን ምስሎች በቀለም ቀቡ




መልመጃ -2፡

1. በደብተራችሁ ላይ ሁለት የጎነ ሦስት ምስሎችን ፣ ሁለት የጎነ አራት ምስሎችን እና ሁለት የክብ ምስሎችን በመሳል ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

2. ከዚህ በታች ለተገለጸው ምስል የሚመሳሰሉ ቅርፆችን አንድ አይነት ቀለም በመቀባት ግለጹ፡፡



3. ካጠብጣቦችን በማያያዝ አድምቁ




7.3 ምስሎችን በስም መዘርዘር


መግቢያ፡ በዚህ ክፍል የባለ ሁለት አውታር ምስሎችና ስሞቻቸውን እንዲሁም የባህሪይ መለያቸውን መግለፅ እንማራለን ::

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የባለ ሁለት አውታር ምስሎችን የባህሪ መለያን በራሳችሁ ቋንቋ ትገልፃላችሁ::




የባለ ሁለት አውታር ምስሎችና ስሞቻቸዉ

ምስሎች	ስም
	ሳነ ሦስት
	ካሬ
	ሬክታንግል
	ሳነ አምስት

	ጎነ ስድስት
	ዳይመንድ
	ሞላላ

መልመጃ -3፡

1. በስተቀኝ በኩል ያሉትን ቁሶች ከተመሳሳይ በስተግራ ካሉ ቅርጻቸው ጋር አዛምዱ።።

ሀ.		
ለ.		
ሐ.		
መ.		

2. የሚከተሉትን ምስሎች ስም ጥሩ። እንዲሁም ባዶ ቦታዎች ላይ ስማቸውን ፃፉ።

ሀ. 

_____

ሐ. 

_____

ሠ. 

_____

ለ. 

_____

መ. 

_____

3. ነጠብጣቦችን በማያያዝ የምታገኙትን ምስል በስም ግለፁ

ሀ. 

_____

ለ. 


_____

ሐ. 

_____

መ. 

_____


ሠ. 

ረ. 

7.3.1 ሬክታንግል

ሬክታንግል አራት ጎኖች አሉት። ሁለት ጥንድ ተቃራኒ ጎኖቹ እኩል ናቸው።


ለምሳሌ ቀጥሎ ያለው ምስል ሬክታንግል ይባላል።



ከላይ ያለው ሬክታንግል ሀለሐመ በመባል ይጠራል። በሌላ መንገድ ሬክታንግል ሀመሐለ፣ መሐለሀ፣ ሐለሀመ በማለት መሰየም ይቻላል።


7.3.2 ጎነ ሦስት

ጎነ ሶስት ሶስት ጎኖች አሉት። ከዚህ በታች ያለው ምስል ጎነ ሶስት ይባላል። ጎነ ሶስት ሀለሐ ተብሎ ይጠራል። ይህን በምልክት ስንጽፍ Δሀለሐ ይሆናል።



7.3.3 ካሬ


ካሬ አራት ጎኖች አሉት የሁሉም ጎኖች ርዝመት እኩል ነው።



ካሬውም ሲጠራ ካሬ ሀለሐመ ይባላል።

7.3.4 ክብ

ቀጥሎ የተገለጸው ምስል ክብ ይባላል።



መ የክብ እምብርት ይባላል። ይህ ክብ ሲጠራ ክብ መ ይባላል።

መልመጃ -4፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1. የጥቁር ሰሌዳ ቅርጽ የሚመደበው በየትኛው ነው?

   ሀ. በጎነ ሦስት ለ. በጎነ አራት ሐ. በክብ

2. ከሚከተሉት አንዱ አራት ጎኖች አሉት?

   ሀ. ካሬ ለ. ክብ ሐ. ሞላላ

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሒሳብ መፅሐፋችሁ ምን አይነት ቅርፅ እንዳለዉ ግለፁ?
2. የክፍላችሁ ወለል ከየትኛዉ ምስል ጋር ይመሳሰላል?
3. ወረቀት በመጠቀም ከዚህ በታች ያሉ ምስሎችን አስመስላችሁ ቆርጣችሁ አውጡ፡፡

ሀ.



ለ.




ሐ.





መ.



4. በመኖሪያ አካባቢያችሁ ከእነዚህ ምስሎች ጋር የሚመሳሰሉ ነገሮች ካሉ ዘርዝሩ፡፡
5. ከሚከተሉት ምስሎች መካከል የትኞቹ ጎነ ሦስት የትኞቹ ጎነ አራት እና የትኞቹ ክብ እንደሆኑ ለዩ፡፡

ሀ. 


ለ. 

ሐ. 


መ. 

ሠ. 

ረ. 


ሰ. 

ሸ. 


ቀ. 

6. ነጠብጣቦችን በማያያዝ የሚገኘውን ምስል በመለየት ግለጹ፡፡

ሀ. 

ለ. 

ሐ.



መ.





ሠ.






ረ.



7. በግራ በኩል ያሉትን ቅርፆች በቀኝ በኩል ካሉት የቅርፆች ስም ጋር አዛምዱ።

	ሳነ አራት
	ሳነ አምስት

	ክብ
	ሞላላ
	ጎነ ሦስት
	ጎነ ስድስት

ምዕራፍ-8

ሥርዓተ ጥለት

መግቢያ፡ የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርፆችን ቀላል ድርድር ወይም ደጋግሞ መጣል ፣ደጋግሞ መጣልን በማስቀጠል እንዲሁም አምሳያ ደጋግሞ መጣል በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይተው ይረዳሉ፡፡
- ቀላል ተደጋጋሚ ጥለቶችን ይመሰርታሉ፡፡

8.1 ደጋግሞ መጣል

መግቢያ፡ የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርፆችን ቀላል ድርድር እንደየ አጀማመራቸው በመመልከትና በማጤን መደርደር ይቻላል፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይታችሁ ከተረዳችሁ በኋላ አምሳያቸዉን ከሁለት በላይ በመድገም ታስቀምጣላችሁ፡፡

ተግባር-1

ምስሎቹን በማየት ቀጥሎ የሚመጣውን ምስል ገምቱ

ሀ)     _____ _____

ለ) 

መልመጃ-1፡

የቅርፆችን ምስል በማየት በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ላይ ደግማችሁ ሳሉ

ምሳሌ፡ 


ሀ) 

ለ) 

ሐ) 

መልመጃ -2፡

ከዚህ በታች ደጋግሞ የተጣሉ ተመሳሳይ ምስሎችን በተመሣሣይ ቀለም በመቀባት አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡ 

ሀ 

ለ 

8.2 ደጋግሞ መጣልን ማስቀጠል

መግቢያ፡ የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርጾችን ቀላል ድርድርን በመመልከት ተከታታይ የድርድር ዋጋዎችን ማግኘት ወይም የጎደሉ የድርድር ዋጋዎችን መስራት ይቻላል። የሚከተሉትን ተግባራት እና አስረጂዎች ተመልከቱ ።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይታችሁ ከተረዳችሁ በኋላ ተከታይ ዋጋቸዉን ታስቀምጣላችሁ።።

ተግባር -2፡

የሚከተሉትን ተከታታይ ቅርፆችን ተከትለው የሚመጡ ቅርፆችን ምስል ሳሉ።።

ሀ) 

ለ) 

መልመጃ -3:

በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ምስሎች አቀማመጥ በማጥናት ቀጥሎ የሚመጣውን ምስል ስላችሁ አሳዩ፡፡

ሀ					—	—	—	—
ለ					—	—	—	—
ሐ					—	—	—	—

8.3 አምሳያን ደጋግሞ መጣል

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- **ቀላል ተደጋጋሚ ጥለቶችን ትመሰርታላችሁ፡፡**

ተግባር-3፡

ከዚህ በታች ያሉትን ተከታታይ ቅርፆች በመመልከት ባዶ ቦታውን ሊተካ የሚችል ቅርፅ ሳሉ፡፡



መልመጃ -4፡

1. የሚከተሉትን ደጋግሞ መጣልን በመመልከት የጎደለውን ሙሉ


ሀ)



ለ)



ሐ)



መ)



2. የሚከተሉትን ቁጥሮች አቀማመጥ በማጥናት ቀጥሎ የሚመጣውን ቁጥር በባዶ ሳጥኑ ሙሉ፡፡

2	4	6	8	10	12	

4	8	12	16	20	24	———
5	10	15	20	25	30	———
3	6	9	12	15	18	———

የማጠቃለያ መልመጃ

1. ከዚህ በታች ደጋግሞ የተጣሉ ምስሎችን ቀቡ

ሀ. 


2. የቅርፆችን ምስል በማየት በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ላይ ደጋግማችሁ ሳሉ

ሀ. 

ለ. 

3. የሚከተሉትን ደጋግሞ መጣልን በማስቀጠል ባዶ ቦታውን ሙሉ

ሀ)




ለ)



4. የሚከተሉትን ደጋግሞ የተጣሉትን ምስሎች በመመልከት የጎደለውን ምስል አሚሉ

ሀ



ለ



ምዕራፍ-9

የርዝመት፤የክብደትና የመጠን መለኪያ

መግቢያ፡ በተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች ርዝመትን፣ክብደትንና መጠንን ለመለካት ልማዳዊ መሥፈሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ሣይንሳዊ መሣሪያወችንም በመጠቀም የቁሶችን ርዝመት፣ክብደትና መጠን መለካት ይቻላል፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ርዝመትን፤ክብደትንና ይዘትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ መለኪያዎች ይለካሉ፡፡
- በርዝመት፤በክብደትንና በይዘት መለኪያዎች ልኬቶችን ያነፃፅራሉ፡

9.1 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ

መግቢያ፡ በአንድ አንድ አካባቢዎች ሰዎች ርዝመትን ለመለካት ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ርዝመትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ በመጠቀም ይለካሉ



ተግባር-1



የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ

1. ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ የምንላቸውን ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለቡድናችሁ አባላት አብራሩ፡፡

2. ርዝመትን ለምን እንለካለን?

በተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች ርዝመትን ለመለካት ከሚጠቀሟቸው ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎች ጥቂቶቹን እንመልከት።

	
ስንዝር	እርምጃ

	
ክንድ	ጫማ

መልመጃ–1

1. የተቀመጣችሁበትን ወንበር በክንዳችሁ ለኩ። ስንት ክንድ ሆነ?
2. የክፍላችሁን ወለል ከጫፍ እስከ ጫፍ በእርምጃችሁ ለኩ። ስንት እርምጃ ሆነ?
3. ከሒሳብ መፅሐፋችሁና ከሒሳብ ደብተራችሁ መካከል የትኛዉ ይረዝማል? የትኛዉስ ያጥራል?

9.2 ርዝመትን ማነፃፀር

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሣይንሳዊ የርዝመት፤ የክብደትና የይዘት መለኪያን በመጠቀም ርዝመትን፤ክብደትንና ይዘትን መለካት ይችላሉ

የቁሶችን ርዝመት በልማዳዊ የርዝመት መለኪያ ወይም በሚይንሳዊ የርዝመት መለኪያ ሚንቲ ሜትር እና ሜትርን በመጠቀም አጭርና ረዥም በማለት ርዝመትን ማነፃፀር እንችላለን።

ተግባር-2

1) የደብተራችሁን ርዝመትና የእስኪሪብቲችሁን ርዝመት በስንዝራችሁ ለኩ። ከሁለቱ ርዝመት የትኛዉ ይበልጣል?
2) ከአምስቱ የእጃችሁ ጣቶች መካከል ረዥሙ የትኛዉ ነዉ? አጭሩስ የትኛዉ ነዉ?

3) ሀ.

ለ.


ከ "ሀ" እና ከ "ለ" የትኛዉ መሥመር አጭር ነዉ?


የትኛዉ መሥመር ደግሞ ረዥም ነዉ?

ምሳሌ፡


1. የሁለቱን ምስሎች ቁመት ተመልከቱ

   የ ሀ ምስል ረዥም ይባላል። የ ለ ምስል ደግሞ አጭር ይባላል።

   ሀ. 

   ለ. 


2. ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የምትመለከቷቸው ሁሉም የ "ሀ" ምስሎች ረዥም ሲሆኑ ሁሉም የ "ለ" ምስሎች ደግሞ አጭር ናቸው።



ርዝመትን በሣንቲ ሜትርና በሜትር መለካት

ሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያዎችን በመጠቀም ርዝመትን መለካት እንችላለን፡፡ ሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያ አሃድ የምንላቸዉ ሜትር፣ ሣንቲ ሜትር ወዘተ የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

ከዚህ በታች የምትመለከቱት ባለ አንድ ሜትር ማስመሪያ ወይም 100 ሣንቲ ሜትር ማስመሪያ ነው፡፡



ምሳሌ፡- ማስመሪያውን በመጠቀም የጠረጴዛውን ርዝመት ለኩ፡፡



ስለዚህ ከላይ ከሥዕሉ እንደምትረዱት የጠረጴዛው ርዝመት 80 ሣንቲ ሜትር ነው።።

ማስታወሻ

1. ሜትርና ሣንቲ ሜትር መካከለኛ እና አጫጭር ርቀትን ወይም ርዝመትን ለመለካት የምንገለገልባቸው ምድቦች ናቸው።።
2. ሜትር በአጭሩ ሲፃፍ **ሜ** ሲሆን ሣንቲ ሜትር ደግሞ **ሣ.ሜ** ብለን በመፃፍ መግለፅ እንችላለን ።።
3. 1 ሜትር ከ100 ሣንቲ ሜትር ጋር እኩል ነው።።

ተመሳሳይ አሃድ ያላቸውን ምድቦች መደመርና መቀነስ

ምሳሌ፡

1. ደምሩ

   ሀ) 50ሣ.ሜ $+$ 30ሣ.ሜ $=$ 80ሣ.ሜ ይሆናል።።

   ለ) 10ሜ $+$ 10ሜ $=$ 20ሜ ይሆናል።።

2. ቀንሱ

   ሀ) 90ሣ.ሜ $-$ 45ሣ.ሜ $=$ 45ሣ.ሜ ይሆናል።።

   ለ) 75ሜ $-$ 5ሜ $=$ 70ሜ ይሆናል።።

መልመጃ–2

በምሳሌው መሰረት አስሉ፡፡

1. 80ሣ.ሜ + 20ሣ.ሜ = _____
2. 50ሣ.ሜ – 20ሣ.ሜ = _____
3. 5ሜ + 5ሜ = _____
4. 1ሜ + 2ሜ = _____

9.3 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች


- ክብደትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ በመጠቀም ይለካሉ

ልማዳዊ የክብደት መለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ ቁሶችን ክብደት መለካት ይቻላል፡፡

የቡድን ሥራ –1


1. ልማዳዊ የክብደት መለኪያ የምንላቸው አነማናቸው?
2. ክብደትን ለምን እንለካለን?
3. ክብደትን በምን መለካት እንችላለን?

ምሳሌ፡ በልማዳዊ የክብደት መለኪያ ክብደታቸውን አነፃፅሩ፡፡



ከልማዳዊ የክብደት ሚዛኑ እንደምንረዳው የምስል ሀ ክብደት ከምስል ለ ክብደት ያነሰ ሲሆን የምስል ለ ክብደት ደግሞ ከምስል ሀ ክብደት የሚበልጥ መሆኑን ያሳየናል።

2.



ከልማዳዊ የክብደት ሚዛኑ እንደምንረዳው የኤሊዋ ክብደት ቀላል ሲሆን የጥንቸሏ ክብደት ደግሞ ከባድ መሆኑን ያሳየናል።

9.4 ክብደትን ማነፃፀር


ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሣይንሳዊ የርዝመት፤ የክብደትና የመጠን መለኪያን በመጠቀም ርዝመትን፤ክብደትንና መጠንን መለካት ይችላሉ

የተለያዩ ቁሶችን ክብደት በልማዳዊ የክብደት መለኪያ ወይም በሣይንሳዊ መሥፈሪያ በመጠቀም ማነፃፀር ይቻላል።

ከዚህ በታች በእያንዳንዱ ሳጥን ዉስጥ ሁለት ሁለት ምስሎች ተቀምጠዋል።

ከምስል “ሀ” እና ከምስል “ለ” የትኛዉ ምስል የሚከብድ ይመስላችኋል?

1. ሀ.  ለ. 	2. ሀ.  ለ. 
3. ሀ.  ለ. 	4. ለ. ሀ. 

አስተዉሉ፡ ከላይ በሰንጠረዡ አንደምትመለከቱት

1. በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለዉ የ“ሀ” ምስል ክብደት ከ“ለ” ምስል ክብደት ይበልጣል።
2. በተራ ቁጥር 2 ላይ ያለዉ የ“ሀ” ምስል ክብደት ከ“ለ” ምስል ክብደት ያንሳል።
3. በተራ ቁጥር 3 ላይ ያሉት የ“ሀ” ምስል ክብደት እና የ“ለ” ምስል ክብደት እኩል ናቸዉ።
4. በተራ ቁጥር 4 ላይ ያለዉ የ“ሀ” ምስል ክብደት ከ“ለ” ምስል ክብደት ይበልጣል።


ምሳሌ:

በምስሉ አንደምትመለከቱት በሚዛኑ ላይ የአንበሳዉ ምስል ከጦጣዋ ምስል ዝቅ ብሎ ወይም የጦጣዋ ምስል ከአንበሳዉ ከፍ ብሎ እናያለን። ይህ ማለት የአንበሳዉ ክብደት ከጦጣዋ ክብደት ይበልጣል ማለት ነዉ። ወይም የጦጣዋ ክብደት ከአንበሳዉ ክብደት ያነሰ መሆኑን ያሳየናል።



መልመጃ– 3

የሚከተሉትን ጥንድ ምስሎች ከባድ ወይም ቀላል በማለት ለዩ።







ኪሎ ግራምንና ግራምን በመጠቀም ክብደትን መለካት

ከዚህ በታች የምትመለከቷቸው ሣይንሳዊ የክብደት መለኪያዎች ናቸው። ክብደታቸዉንም ከለካን በኃላ የምናገኘዉን ዉጤት በኪሎ ግራም ወይም በግራም እንገልፃለን። ስለዚህ ሣይነሳዊ የክብደት መለኪያ አሃዶች የምንላቸው ኪሎግራም፣ ግራም ወዘተ ናቸዉ።

ሣይንሳዊ የክብደት መለኪያዎች





ማስታወሻ

1. ኪሎ ግራም በአጭሩ ሲፃፍ ኪ.ግ ሲሆን ግራም ደግሞ ግ ብለን በመፃፍ መግለፅ እንችላለን ።
2. ኪሎ ግራም ከግራም ይበልጣል።

ተመሳሳይ አሃድ ያላቸውን ምድቦች መደመርና መቀነስ

ምሳሌ፡

1. ደምሩ

   ሀ. $2ኪ.ግ + 3ኪ.ግ = 5ኪ.ግ$ ይሆናል።

   ለ. $50ግ + 12ግ = 62ግ$ ይሆናል።

2. ቀንሱ

   ሀ. $85ኪ.ግ - 50ኪ.ግ = 35ግ$ይሆናል።

   ለ. $70ግ - 20ግ = 50ግ$ ይሆናል።

መልመጃ–4

በምሳሌው መሰረት አስሉ፡፡

1. $13ኪ.ግ - 3ኪ.ግ = _____$
2. $11ኪ.ግ + 11ኪ.ግ = _____$
3. $33ግ - 5ግ = _____$
4. $55ግ - 25ግ = _____$
5. $60ግ + 15ግ = _____$

9.5 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የመጠን መለኪያ

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ይዘትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ የመጠን መለኪያ በመጠቀም ይለካሉ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች የሚጠቀሟቸውን የመጠን መለኪያዎችን ወይም መስፈሪያዎችን እንመለከታለን፡፡

ተግባር –3

1. በአካባቢያችሁ ልማዳዊ የመጠን መለኪያ የሚባሉትን ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ያገኛችሁትንም መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

በሰንጠረዡ የምትመለከቷቸው መጠንን ለመለካት የምንጠቀማቸዉ ልማዳዊ የመጠን ወይም የይዘት መለኪያዎች ናቸው፡፡

ሀ. 	ለ. 
ሐ. 	መ. 

9.6 መጠንን ማነፃፀር

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሣይንሳዊ የርዝመት፤ የክብደትና የመጠን መለኪያን በመጠቀም ርዝመትን፤ክብደትንና መጠንን መለካት ይችላሉ

ልማዳዊ የመጠን መሥፈሪያን ወይም ሊትርን በመጠቀም የቁሶችን የመያዝ አቅም ማወቅ እንችላለን፡፡

ተግባር–4

1. ከሻይ መጠጫ ብርጭቆና ከዉሃ መጠጫ ብርጭቆ የትኛዉ የበለጠ ፈሳሽ መያዝ ይችላል?

2. አንድ ጀበና ቡና ሰንት ሲኒ ቡና መያዝ ይችላል? ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

ምሳሌ፡ የትኛዉ ምስል ብዙ ፈሳሽ መያዝ ይችላል?

1. ሀ. ለ.





ምስል "ለ" ከምስል "ሀ" የበለጠ ፈሳሽ መያዝ ይችላል፡፡

2. ሐ. መ.





ምስል "መ" ከምስል "ሐ" የበለጠ ፈሳሽ መያዝ ይችላል፡፡

3. ሠ. ረ.





ምስል "ሠ" ከምስል "ረ" የበለጠ ፈሳሽ መያዝ ይችላል፡፡

መልመጃ–5

ከአራቱ መሥፈሪያዎች የትኛው ብዙ ፈሳሽ፣ የትኛው ደግሞ አነስተኛ ፈሳሽ መያዝ ይችላል?

ሀ. 	**ለ.** 
ሐ. 	**መ.** 

የፈሳሽን መጠን በሊትር መለካት


የፈሳሽን ይዘት ወይም መጠን በሊትር መለካት እንችላለን፡፡



$^1/_2$ ሊትር የሚይዝ ጆግ



1 ሊትር የሚይዝ ጆግ



1 ሊትር የወተት ጠርሙስ

የፈሳሽ ይዘት መስፈሪያ መሳሪያዎች ወይም ዕቃዎች ናቸው

አስተውሉ፡ ሊትር በአጭሩ ሲፃፍ “ሊ” ተብሎ ይፃፋል፡፡

ምሳሌ፡ 20ሊትር = 20ሊ፣ 15ሊትር = 15ሊ፣ 10ሊትር =10ሊ፣ $\frac{1}{2}$ሊትር = $\frac{1}{2}$ሊ ወዘተ::

ምሳሌ:

1. የሦስቱን ባልዲ ውሃ በአንድ በርሜል ውስጥ ብንጨምር በጠቅላላው ስንት ሊትር ውሃ ይኖረናል?



20 ሊትር ውኃ



20 ሊትር ውኃ



20 ሊትር ውኃ

20ሊ + 20ሊ + 20ሊ = 60ሊ

መልመጃ–6

1. አንድ ሊትር ዉሃ ስንት የሻይ ብርጭቆ ውሃ መያዝ ይችላል? እቤታችሁ አረጋግጡ።
2. 5 ሊትር ውሃ + 5 ሊትር ውሃ = _____ ሊትር ውሃ።
3. 25 ሊትር ውሃ - 5 ሊትር ውሃ = _____ ሊትር ውሃ።
4. አንድ በርሜል 100ሊትር ውሃ መያዝ ቢችልና 20ሊትር መያዝ በሚችል ባልዲ ውሃ እየሞላን ብንጨምርበት አጠቃላይ በርሜሉ ስንት ባልዲ ውሃ መያዝ ይችላል?

የማጠቃለያ መልመጃ

1. አንድ የለስላሳ ጠርሙስ ስንት ሲኒ ወሃ መያዝ ይችላል? እቤታችሁ በመስፈር አረጋግጡ።
2. ከሒሳብ መፅሐፋችሁና ከአንድ የክፍላችሁ ወንበር የትኛዉ ይከብዳል?
3. በአካባቢያችሁ የምታዉቋቸዉን የመጠን መለኪያዎችን ዘርዝሩ?
4. የርዝመት መለኪያ ሜትርን በመጠቀም የክፍላችሁን መጠነ ዙሪያ በቡድን ሆናችሁ ለኩ።ያገኛችሁትንም ዉጤት ለመምህራችሁ አሳዉቁ።
5. ማሥመሪያችሁን በመጠቀም የጠረጴዛችሁን ርዝመት ለኩ። ስንት ሣንቲ ሜትር ሆነ?
6. ደረጀ 16 ሜትር ርዝመት ያለው እንጨት ነበረው ከዚያ ላይ 7 ሜትሩን እንጨት ቆርጦ ለጓደኛው ቢሰጥ ስንት ሜትር እነጨት ይቀረዋል?
7. አበበች ከቧንቧ ውሃ በባልዲ እየቀዳች በርሜል ውስጥ ትጨምራለች። የበርሜሉ ውሃ የመያዝ አቅም 90ሊትር ነው። አበበች አጠቃላይ ወደ ባልዲው የጨመረችው ውሃ 55ሊትር ቢሆን በርሜሉን ለመሙላት ስንት

ሊትር ውሃ ይቀራታል?

8. $65ኪ.ግ + 25ኪግ = ____$

9. $50ግ + 50ግ = ____$

10. $95ግ - 15ግ = ____$

11. $81ሊ - 13ሊ = ___$

12. ታደሰ 26 ኪ.ግ ስኳር ቢኖረውና ከዚያ ላይ 10ኪ.ግ ስኳር ለጓደኛው ቀንሶ ቢሰጥ ታደሰ ስንት ኪ.ግ ስኳር ይቀረዋል?

13. 20ሜ ርዝመት ካለው መንገድና 30ሜ ርዝመት ካለው መንገድ የትኛዉ መንገድ ይርቃል?

14. 50ሊ ውሃ በያዘ በርሜል ውስጥ 25ሊ ውሃ ብንጨምር በአጠቃላይበርሜሉ ውስጥ ስንት ሊትር ውሃ ይኖራል?

ምዕራፍ-10

የኢትዮጵያ ገንዘቦች

መግቢያ፡ የኢትዮጵያ ገንዘቦች ማለት የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና የኢትዮጵያ ሳንቲሞች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ማለት ነው።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የኢትዮጵያ የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ይለያሉ።
- በየኢትዮጵያ የብር ኖቶችና ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ።
- ከምዕራፉ ጋር ተያያዥ የሆኑ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ።

10.1 የኢትዮጲያ ሳንቲሞችና የብር ኖቶች

ሳንቲሞች

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- **የኢትዮጵያን የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ለይተዉ ያዉቃሉ**

የኢትዮጵያ ገንዘብ ምስላቸው ከዚህ በታች የተመለከተው ሁሉ የኢትዮጵያ ሳንቲሞች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ናቸው።

					
አንድ ሳንቲም	አምስት ሳንቲም	አሥር ሳንቲም	ሃያ አምስት ሳንቲም	ሃምሳ ሳንቲም	የአንድ ብር ሳንቲም

አስተውሉ፡ ሁሉም ሳንቲሞች የፊትና የጀርባ ምስሎች አሏቸው።



የ 1 ባለ 5 ሳንቲም ዲናር በ 5 የባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።



የ አንድ ባለ 10 ሳንቲም ዲናር በ 2 የባለ አምሥት ሳንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።



የ አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በ 2 የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።



የ አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በ 5 የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።

የቡድን ሥራ–1

አንድ የቤተሰባችሁን አባል በመጠየቅ የኢትዮጵያን የሣንቲም ገንዘቦች ዓይነትና ምንዛሬ ዘርዝራችሁ ለቡድን አባሎቻችሁ አቅርቡ።

መልመጃ–1

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

ሀ) አንድ ባለ አሥር ሣንቲም ዲናር በስንት ባለ አንድ ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

ለ) አንድ ባለ 25 ሣንቲም ዲናር በስንት ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

ሐ) አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በስንት ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

2. ሠንጠረዡን በምሳሌው መሠረት ሙሉ።

የተሰጡት የሣንቲም ዲናሮች	በባለ 1ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጹ	በባለ 5 ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጹ	በባለ 10ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጹ	በባለ 25ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጹ
50 ሣንቲም	50	10	5	2
25 ሣንቲም				
10 ሣንቲም				
5 ሣንቲም				

የብር ኖቶች

የሚከተሉት የኢትዮጵያ የብር ኖቶች ምሥሎች ናቸው፡፡



የአምስት ብር ኖት



የአሥር ብር ኖት



የሃምሳ ብር ኖት



የመቶ ብር ኖት



የሁለት መቶ ብር ኖት

መልመጃ–2

ሠንጠረዡን በምሳሌው መሠረት ሙሉ።

የተሰጠው የብር ኖት	ምንዛሪ			
	በባለ 5 ብር ኖት	በባለ 10 ብር ኖት	በባለ 50 ብር ኖት	በባለ 100 ብር ኖት
ባለ 200 ብር	40	20	4	2
ባለ 100 ብር				
ባለ 50 ብር				
ባለ 10 ብር				

10.2 የሣንቲሞችና የብር ኖቶች ዝምድና

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በኢትዮጵያ ብር ኖቶችና ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ

የብር ኖቶች በሣንቲሞች ሊመነዘሩ ይችላሉ።

ምሳሌ፡

1) አንድ የ5 ብር ኖት በ 10 የ 50 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዝራል። እንዲሁም ይኸዉ የ 5 ብር ኖት በ 20 የሃያ አምስት ሣንቲም ዲናሮች ሊመነዘር ይችላል።
2) በተመሳሳይ መልክ አንድ የ 10 ብር ኖት በ 20 የ 50 ሣንቲም ዲናሮች ሊመነዘር ይችላል።

የቡድን ሥራ–2

1. የሚከተለዉን ሰንጠረዥ አጥኑ

የብር ኖት	ባለ 1 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 50 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 1 ብር ሣንቲም ዲናር
5		100	50	20	10	5
10			100	40	20	10

2. የሣንቲምና የብር ኖት ሞዴሎችን ከወረቀት ወይም ከሌላ በአካባቢዉ ከሚገኝ ምቹ ነገር ሥሩ።
3. በእነዚህ ሞዴሎች በመጠቀም በምንዛሬዎች ላይ ከላይ ከተሰጠዉ ሠንረዥ ጋር በማዛመድ ተወያዩ።
4. ከላይ በቁጥር 2 ላይ በሰራችሁት ሞዴሎች በመጠቀም ከቡድናችሁ አባላት አንዳችሁ ሻጭ በመሆንና ሌሎቻችሁ ገዢ በመሆን የመማሪያ ቁሳቁሶቻችሁን በ በሻጭና በገዢ መልክ ተለዋወጡ።

   የሚከተሉትን የዋጋ ተመንም ተጠቀሙ።

   1 ደብተር.....13 ብር

   1 የሒሳብ መጽሐፍ.....38 ብር

   1 እርሳስ.....2 ብር

   1 እስክርብቶ.....10 ብር

10.3 ፕሮብሌሞችን መስራት

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በኢትዮጵያ ብር ኖቶችና ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ

ምሳሌ፡-

የአንድ ሳሙና ዋጋ 22 ብር ቢሆን የሁለት ሳሙናዎች ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?

$$\underline{22} \text{ ብር} + \underline{22} \text{ ብር} = \underline{44} \text{ ብር}$$

መልመጃ–3

1. የአንድ ዳቦ ዋጋ 2ብር እና የአንድ ሻይ ዋጋ 1ብር ቢሆን በአጠቃላይ የአንድ ዳቦ እና የአንድ ሻይ ዋጋ ስንት ነው?
2. የአንድ ሳሙና ዋጋ 22 ብር ቢሆንና አንድን ሳሙና ለመግዛት ለባለ ሱቁ 30 ብር ብትሰጥ/ጪ ስንት ብር ይመለስልሃል/ሻል?
3. የ 1 ኪሎ ግራም ሙዝ ዋጋ 18 ብር ቢሆን የ 2 ኪሎ ግራም ሙዝ ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?



ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

1. አንድ የመቶ ብር ኖት

   ሀ) በስንት የ 5 ብር ኖቶች ይመነዘራል?

   ለ) በስንት የ 50 ብር ኖቶች ይመነዘራል?

2. አንድ የ10 ብር ኖት

   ሀ) በስንት የባለ 50 ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

   ለ) በስንት የባለ 25 ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

   ሐ) በስንት የባለ 10 ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

3. አንድ ባለ 5 ብር ኖት

   ሀ) በስንት የባለ 10 ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

   ለ) በስንት የባለ 25 ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

   ሐ) በስንት የባለ 50 ሳንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

ምዕራፍ-11

የኢትዮጵያ ጊዜ

መግቢያ፡ ጊዜ አንድን ተግባር ለማከናወን ወይም ለመፈፀም የሚፈጀውን ቆይታ ለመለካት የሚያገለግል ነው፡፡ ቆይታ በጊዜ ሲለካ መግባበት እንችላለን፡፡ በመሆኑም ሁሉም ሀገራት ጊዜን በመለካት ይጠቀማሉ፡፡ ኢትዮጲያ ቀደምት የሆነ የራሷ የጊዜ መለኪያ ወይም ቀን መቁጠሪያ ካላቸው ሀገራት አንዷ ናት፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በቀንና በሣምንት ውስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያትንና የሰዓት መሥፈሪያ ምድቦችን እንማራለን፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሳምንቱን ቀናት ይገልፃሉ፡፡
- የዕለት ተግባራቸዉን በቅደም ተከተል ይገልፃሉ፡፡

ተግባር-1

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

1. የመኝታ ጊዜያችሁን ግለፁ፡፡
2. ወደ ትምህርት ቤት የምትመጡበትን ጊዜ ግለፁ፡፡
3. ፀሐይ የምትወጣዉ ጠዋት ነዉ ወይስ ማታ?
4. ፀሐይ ከጠለቀች በኃላ ያለዉ ጊዜ ቀን ወይስ ማታ ይባላል? ፀሐይ ወጥታ እያለችስ ያለዉ ጊዜ ምን ይባላል?

11.1 በኢትዮጵያ ቀን ዉስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያት

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- **የእጅ ሰዓት በመጠቀም ጊዜን መግለፅ ይችላሉ**

አንድን ቀን በቡዙ ቦታ ከፋፍለን መግለፅ እንችላለን፡፡ ከእነዚህም ጠዋት፣እኩለ ቀን፣ማታ፣ ሌሊትና እኩለ ሌሊት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

ፀሐይ አንደ ወጥታ፣ ጠልቃ፣ ተመልሳ እስክትወጣ ያለዉ ጊዜ አንድ ቀን ተብሎ ይታወቃል ፡፡ እያንዳንዱ ቀን 24 ሰዓታት አሉት፡፡ የተለያዩ ዓይነት የሰዓት መቁጠሪያዎች አሉ፡፡ ቀጥሉ የሚታዩት የሰዓት መቁጠሪያ ምስሎች ናቸዉ፡፡






ከላይ ያሉት ምስሎች ሁለቱም የሰዓት መስፈሪያ ሞዴሎችን ያመለክታሉ፡፡

የሰዓት መስፈሪያ ሞዴሎች

1) በቀኝ በኩል ያለዉ የሰዓት መቁጠሪያ ስዕል ነዉ። ይህም ዕቃ ሰዓት ይባላል። በዚህ ዕቃ ላይ ወፈር ብሎ አጠር ያለ ጨረር እና ቀጥን ብሎ ረዘም ያለ ጨረር ይታያል።

ረዣዥሙ ጨረር ደቂቃን ያመለክታል።

አጭሩ ጨረር ሰዓትን ያመለክታል።




2) በቀኝ በኩል ያለዉ ምስል የሰዓት መቁጠሪያ ዕቃ ነዉ። ከዚህ ላይ ሰዓትን አንብቦ መናገር ብቻ ነዉ። ለምሳሌ በተሰጠዉ ምስል ላይ 6፡00 ን ያመለክታል።ሲነበብም ስድስት ሰዓት ተብሎ ነዉ።



መልመጃ–1

1) የሚከተሉት የሰዓት ሞዴሎች ስንት ሰዓት እንደሚያመለክቱ ግለፁ።

ምሳሌ-1፡ በተሰጠው የሰዓት ምስል ላይ የሰዓት ቆጣሪው 5ን ያመለክታል። የደቂቃው ደግሞ 12ን ያመለክታል። ስለዚህ 5 ሰዓትን ያመለክታል።



ሲነበብ 5 ሰዓት ሲፃፍ



ሀ) 

ለ) 

ሐ) 

መ) 

ሠ) 


ረ) 

ሰ) 




ሸ) 

ቀ) 

2) ከዚህ በታች ያሉትን የሰዓት ምስሎች ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የሚታገኙትን ሰዓት በምስሉ ላይ አስቀምጡ። **ምሳሌ፡**



ከ 2 ሰዓታት ቀጥሎ

ሀ		ለ)	
ሐ		መ	

11.2 የሣምንቱ ቀናት

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሳምንቱን ቀናት መግለፅ ይችላሉ

ከላይ አንድ ቀን በ24 ሰዓታት እንደሚከፋፈል አይተናል ። ይህም ማለት 24 ሰዓት አንድ ቀን እንደሚሆን ያሳያል።

በተመሳሳይ 7 ቀናት አንድ ሳምንት ይሆናሉ። የሳምንቱም ቀናት የየራሳቸው ስም አሏቸዉ።

የሚከተሉት የሳምንቱ ቀናት ናቸው። እነሱም ሰኞ፣ማክሰኞ፣ረቡዕ፣ሐሙስ፣

ዓርብ፣ቅዳሜ እና እሁድ ናቸው።

የቡድን ሥራ–1

- የሳምንቱን ቀናት የሚገለፅ መዝሙር በቡድን ሆናችሁ ዘምሩ።

መልመጃ–2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1. ሁለት ቀኖች ስንት ሰዓቶች ይሆናሉ?
2. ሁለት ሳምንቶች ስንት ቀኖች ይሆናሉ?
3. ከማክሰኞ ቀጥሎ የሚመጣው የሳምንቱ ቀን ማን ተብሎ ይጠራል?
4. ከእሑድ በፍት ያለው የሳምንቱ ቀን ማን ተብሎ ይጠራል?
5. ዛሬ ሰኞ ከሆነ ነጌ ቀኑ ምን ይሆናል?
6. ዛሬ ቀኑ እሁድ ቢሆን ትላንት ቀኑ ምን ተብሎ ይጠራል?

11.3 የቃላት ፕሮብሌሞች

ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ጊዜን የተመለከተ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ።

ምሳሌ:-

ሶስት ሳምንቶች ስንት ቀናት አላቸው?

ሶስት ሳምንት = 1 ሳምንት + 1 ሳምንት + 1 ሳምንት

= 7 ቀናት + 7 ቀናት + 7 ቀናት

= 21 ቀናት

መልመጃ–3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. ሶስት ቀናት ስንት ሰዓት ይሆናል?
2. 3 ቀናት + 2 ቀናት = _____ ቀናት።
3. 2 ሳምንት + 2 ሳምንት = _____ ቀናት።
4. 1 ቀን + 1 ቀን = _____ ሰዓት

የማጠቃለያ መልመጃ

አዛምድ

1	5:00	ሀ) 
2	7:00	ለ) 

3	6:00	ሐ) 
4	1:00	መ) 
5	4:00	ሠ) 